# መሬት የማን ነው?

ከአቤ ጉበኛ

Niguss
Digital Library

# መሬት የማን ነው?

ከአቤ ጉበኛ

አዲስ አበባ

፲፱፻፶፪ ዓ/ም

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

# ማውጫ

መነሻ።3
ክፍል ፩4
ክፍል ፪7
መግቢያ9
ኢትዮጵያውያን ድርሻ።16
የጢሰኞኖች ድርሻ17
የሰሜናዊ ሕዝብ ድርሻ18
አቤ ጉበኛ።20
የችግሩ ምክንያቶች20
ስለ አሠፋፈሩና ስለ አሠራሩ ዘዴ29
የሕዝቡን አሠፋፈርና የአሠራር ዘዴ ስለመለወጥ33
የማስተማሪያው ዋና ዘዴ35
የተለየ ኃላፊነት ያለባቸው ክፍሎች36
፪ኛ ቤተ ክርስቲያናችን ኃላፊእነት አለባት38
፫ኛ ወጣቶች ታላቅ ኃላፊነት አለባቸው39
፬ኛ እያንዳንዱ ያገር ቤት ኗሪ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት40
ግባችን40
ወደ ግባችን የምንጓዝባቸው መንገዶች።43
መድረሻ49
ስለደራሲው በጥቂቱ**Error! Bookmark not defined.**

# መነሻ፡፡

በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም በጥቅምት ወር ማለቂያ ላይ ከታተመው «የሮም አወዳደቅ» ከሚለው መጽሐፌ የተወሰደ፡፡

# ክፍል ፩

ነጋዴ - ዛሬ አንተ ገበሬ በጣም ወስልተኻል ብርቱ ነው ጥፋትህ በህል መውቂያ ወራት ሥራን ሁሉ ትተህ

ከተማ መምጣትህ!

ገበረ- እኔ ምን ቸገረኚ በዋለበት ቢቀር ቢወድም ቢጠፋ እኔ እድለ-ቢሱ ክረምቱን በዝናም በጋውን

በሐሩር ብማስን ብለፋ የሮም ባላባት ልጅ በሰው ተደግፋ በሀገራችን ሀብት ደግሞም በኛ ድካም ሥቃይ በሞላበት ከቤቷ ሳትወጣ እስዋ ለብቻዋ ዓለም ዐየችበት።

እኔ ግን ለፍቼ በጋውን በሐሩር ክረምቱን በጭቃ

እንኳን ለሌላ ሀብት ለዕለት ትዳሬም አልቻልሁም ልበቃ።

ነጋዴ - ምንም ሥቃይ ቢሆን ያው ይሻላል

እንጂ የግብርናው ሥራ

የንግዱማ ነገር እንደ ቀረ ይቅር

ተወው አይወራ!

ገበሬ - አዬ የሰው ነገር! ለካ የለም ፍጡር

የፈጠረ አምላኩን የሚያመሰግን

አሁን ያንተው ጩኸት ደግሞስ

ማማረሩ ስለምን ይሆን?

ነጋዴ - ሁሉም በያለበት ይገፋ ይሆናል

ምናልባት አላውቅም!

ግን አለ እንዳይመስልህ በአሁኑ

ዘመን ውስጥ ነግዶ መጠቀም!

ባታውቀው ነው እንጂ የዛሬውን
ዘመን የነጋዴ ሥራ
የታከሱ የግብሩ የጽዳቱ ጉቦ ሥቃዩ
መከራ
ደግሞ ከዚህ በላይ ገበያው የሞተ
ሁል ጊዜ ኪሣራ
በዚህም ተናደህ ጥቂት ብትናገር
ታፍሰህ ትጓዛለህ ከተረፈችህ ሀብት
ከጥሪትህ ጋራ!
ገበሬ - መጉዳቱ ባይቀር ግፍም መቀበሉ
ሁሉም ባለበቱ
የገበሮች ሞት ግን ከሁሉም ልዩ
ነው ሲአል ነው በውነቱ
ሹሙ አገረ ገዥ ቆሮው ባላባቱ
ሥራን የማይወደው እኔ ጌታ - ነኝ
ባይ ወይ ዘር ቈታሪው ጨዋኙ
ሙብዛቱ!
የሁሎችም ሥራ ያው የተለመደው
አንድ ነው ብልሐቱ
ሲያላግጡ መኖር ንጹሑን ገበሬ
ሲያሥሩና ሲፈቱ።
ነጋዴ - አንተንስ የሚያዝህ ያገርህ ባላባት
ወይንም ገዢህ ነው

እኔን የሚያስቸግር የሚያሠቃየኝ

ግን ደሀ ነው እንደኔው

ነገር ሥራ ተብሎ ተቀጥሮ የሚ

ኖር አንዱንም ሳያውቀው።

ገበሬ - ቂል ነህ ልበልህ!

ነጋዴ - እንዴት?

ገበሬ - ከተኵላና ከጅብ ማናቸው ቢበላህ ይሻልኻል?

ነጋዴ - ማንኛውም አውሬ እንዲበላኝ አልፈልግም

አውሬ እንዲበላኝ ከፈለግሁ ግን

ሁሉም በገጠጠ ጥርሱ ነው የሚያነክተኝ!

ታዲያ ላውሬ ጥርስ የተኵላ

ሆነ የጅብ ምን ምርጫ አለው?

ገበሬ - ይኸን ካወቅህስ እኔም ያልሁህ

ይኸን ነው አንተን ከበደለህ ባላባት

አገረ ገዥ ሹም ተራ ሰው ቢሆን

ምን ልዩነት አለው?

ነጋዴ - እውነትህን ነው እኔው ራሴ ተሳስቼ? ነው።

# ክፍል ፪

ጢባርዮስ - እናንተ ወንድሞቼ በዛሬው ቀጠሮ

እዚህ ተሰብስበን እንድንመካከር ስል

የነገርኋችሁ

ማልኮስ- የባሮች ነፃነት ተወርቶ እንደሆነ

ሁላችን ጭጭ ተወርቶ አድምጡ

እባካችሁ!

አብድናጐ - እኔም ይመስለኛል የሚነግረን ጉዳይ

ይኸም ሳይሆን አይቀር።

ገበሬ - ቆይኮ ይናገር!

ነጋዴ - ነፃነት ከሆነ መቼ ይለያሉ ጢሰኛና ገባር።

ጢባርዮስ - እስኪ ቆዮኝ!

እስከዚህ ድረስ ነፃ ሕዝብ በመሆን

ሠርቶ ለመጠቀም በውነት ካማራችሁ

ነፃነት እዚህ ነው ያለ ከደጃችሁ።

ነጋዴ - አዬ! ለካስ ሞኝ ነህና! ጌታው

ሲኞር ጢባርዮስ ታላቅ ሰው ነህ

ብዬ ሳምንብህ በውነት።

እስኪ አምላክ ያሳይህ ባገር መኖር

ብቻ ይባላል ነፃነት?

ብዙ ሀብት ታሽጎ ባገራችን መሬት

ሮማውያን ሁሉ ሠርተን በመጠቀም

እንዳንኮራበት

ሰብስቦ በመያዝ አትድረሱ ሲለን

አንዳንዱ ባላባት!

ገበሬ - እባክህ ወንድሜ ጉዳቴን ልናገር

ለኔ ምንም የለኝ ሌላው ሁሉ

ቀርቶ ቤት የምሠራበት

ወይም እንኳ ትንሽ ከብት

የማቆምበት።

ነጋዴ - ቆይኮ ታገሠኝ ነገሬን ልጨርስ።

ገበሬ - እስከ መቼ ድረስ?

ጢባርዮስ - እኔ እንዳልናገር ያሰብሁትን ነገር

ጊዜውን ጨረሰው የናንተው ክርክር።

፩ኛ ሰው - እባካችሁ ቆዩ! ሲኞር ጢባርይዮስ

እንደጀመሩልን ሁሉን ይናገሩ።

ለድሆቹ ድጋፍ ሳይሆን እንደ

ማይቀር ገና ከቅድሙ ገብቶኛል

ምሥጢሩ!

፪ኛ ሰው - እኔንም ገብቶኛል!

፫ኛ ሰው - ከሁላችሁ ይልቅ እጅግ በጣም

እርጎ ቅድሙን ታውቆኛል።

ጭቆና ይቅርና ደህም በሀገሩ በነፃ

ነት ይኩራ ያሉ ይመስለኛል!

፩ኛ ሰው - አማልክት ይባርኩህ ነገሩ ገብቶኻል

እኔም እስማማለሁ!

ይህን አሰባችሁ ተብሎ ሞት ቢመጣ

በርግጥ እሞታለሁ።

፫ኛ ሰው - እኔም እሞታለሁ ስለዚህ ነገር!

ደግሞ አትጠራጠር።

ማልኮስ - እኔስ በጣም ፈራሁ ስለሁኔታችሁ

ሁላችሁ ባንድ ቀን ሙታችሁን

ሙታችሁ

መሬት የት ሊገኝ ነው ለመቃብራችሁ?

አብድናጐ - እርግጥ ነው! መሬታችሁ ሁሉ የአገራችሁ አፈር

ለጥቂት ሀበታሞች ጥንት የተሰጠ ነው!

# መግቢያ

«መሬት ለአራሹ» የሚል መዝሙር እየዘመሩ ተማሪዎቻችን ብዙ ዓመታት አልፈዋል። በደቡባዊ ኢትዮጵያ በብዛት የሚገኙ ጢሰኞችን አሳዛኝ የኑሮ ሁኔታ የተደረሱ ወጣቶች ይህን ማድረጋቸው የሰውነትና የኢትዮጵያዊነት ተግባራቸው ነው።

ይህ ነገር ያስጨነቀው እነሱን ብቻ አልነበረም። ከነሱ መነሣት በፊትና ከዚያም በኋላ ብዙ ሰዎች ለዚህ ጉዳይ ታግለዋል። በራሴም በኩል በየመጽሐፎቼ የመንግሥቱንና የግፈኞች ባለሥጣኖኙን መጥፎ ተግባር ሳጋልጥ የጢሰኞችን ችግርና መከራ ሳልጠቅስ ቀርቼ አላውቅም።

ለምሳሌ ከዛሬ አሥር ዓመታት በፊት ጽፌ ባሳተምሁት «ሰይፈ ነበልባል» በተባለው መጽሐፌም ስለከተማና ገጠር መሬቶች ይዞታ የሚከተለውን ሐሳብ ገልጬ ነበር።

«ሌሎች መንግሥታት ያገራቸው መሬት ሲጠብ ለተቸገረው ሕዝባቸው በቂ ቦታ ለማግኘት የሌሎችን ወሰን እየገፉ ጦርነት እስከ ማንሳት ይደርሱ ነበር።

እኛ ግን አንዳንድ ባለጥቅሞች በስም የያዙትን የሀገራችን መሬት አደላድለን የመሬት ዕጦት ላስቸገራቸው የሀገራችን ሕዝቦች ማከፋፈል አቅቶት እንጨነቃለን።

መሬታችን ሁሉ መሥራት ለሚችሉና የሀገሪቱ ተወላጆች ለሆኑ ተከፋፍሎ ተሰጥቶ በሥራ ላይ ማዋል እንጂ በአንዳንድ ሰዎች ስም ቦዝኖ መቀመጥ የለበትም።

የአንዳንድ ሰዎችን ቍጣ እየፈራን የሀገችንን ጠቅላላ ጥቅም የሚጎዳ ነገርን ዝምብለን ማየት የለብንም።

፩ኛ/ ለርሻ የሚሆኑ መሬቶች ሁሉ ለሀገራችን ገበሬዎች ይደለደላሉ። የጢሰኛና የገባር ታሪክም በዚህ ያልቃል።

፪ኛ/ በታወቀ ጊዜ በገንዘብ ሳይገዛ በልዩ ልዩ የማጭበርበር ምክንያት ብዙ የከተማ ቦታ የያዘ ከሁለት ቤቶች በላይ ያለው በቦዘን ያስቀመጠው ቦታ ቢገኝ መንግሥት የቤት መሥሪያ ገንዘብ እያለው መሬት ለሌለው ሰው ይሰጣል።

፫ኛ/ ማንኛውም ሰው መንግሥት ሳያውቅ ከአንድ የተቸገረ ሰው መሬት መግዛት ሻጩም መሸጥ አይፈቀድለትም።

፬ኛ/ በተራድኦ ለተቋቋመ የርሻ ድርጅት ካልሆነ በቀር ለአንድ ሰው ቢበዛ ከሁለት ጋሻ የበለጠ መሬት አይፈቀድለትም።

፭ኛ/ አንድ ሰው ለአካለ መጠን ባልደረሱ ልጆቹ ወይም የሌሎች ልጆች ስም መሬት መካፈል ወይም መግዛት አይችልም።»

ብዙ ሰዎች የዚህን ጉዳይ አሳሳቢነት በየጊዜው ገልጸዋል። ሌላው ቀርቶ ለብዙ የመሻሻል እርምጃዎች የቀረቡ ሐሳቦችን ሁሉ «ጆሮ ዳባ ልበስ» ብሎ

ሲበዛላቸው የኖረው መንግሥት ብዙ ባያሠራውም የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴርን አቋቁሞ ነበር።

ይሁን እንጂ ሁሉም ነገር ሁኖ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ኤክስፐርቶችም አማክረው ምንም መድኃኒት ሳያስገኙለት ቆይተዋል።

ለዚህ ችግር ዋና ጠንቆች ከሆኑት ነገሮች መካከልም እጅግ ጎልተው ለማንም የሚታዩ ታላላቅ ምክንያቶች አሉ። እነሱም

፩ኛ/ ራሳቸው ዋናዎቹ የመሬት ዘራፊዎች ከመሆናቸው በላይ ስለ ሕዝብ ችግር ምንም ስሜት ያልነበራቸው የድሮ ባለሥልጣኖች የለውጡ ፍጹም ተቃራኒ ስለነበሩ

፪ኛ/ ራሱ የመሬቱ ሥሪት ዝብርቅር መሆኑ

፫ኛ/ እነዚያው ታላላቅ የመሬት ዘራፊዎች የነበሩት ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና ግብረ - አበሮቻቸው ለራሳቸው ወገን ለማብዛት ሲሉ የተወሰነ መሬት ያላቸውን ሁሉ በአንድ ላይ አስበርግገው ለማስነሣት በመፈለግ ባለርስት ሁሉ ተነቅሎ ጢሰኛ ብቻ ባለ ርስት ይሆናል የሚል ወሬ ያስነዙ ስለ ነበር

፬ኛ/ ጢሰኞች መንግሥት የራሳቸውን ድርሻ መሬት እንዲሰጣቸው ለመስፈርና ለመቋቋም እንዲረዳቸው በመጠየቅ ፈንታ «እኛ ሰፍረንበት ከተገኘን» አንድ ጋሻም ሆነ ግማሽ ጋሻ አንድ ማሳም ይሁን ያለውን ሌላ ኢትዮጵያዊ እየቀማችሁ ስጡን የሚል ግልጽ አድልዎን ብቻ ሳይሆን ግልጽ ሁከትን የሚፈጥር ተግባር እንዲፈጸምላቸው መፈለጋቸው

፭ኛ/ የሰሜናዊ ኢትዮጵ ክፍለ ሀገሮች ሕዝብ ስለ መሬት ያለው አስተሳሰብ ከሃይማኖት ከቤተ ሰብ ጋር የሚመሳሰል ሁኖ ለራሱ ለሕዝብ ደኅነት ሲባል በሚሞከር የመሬት ጉዳይ ሁሉ ምክንያቱን ለመረዳት እንኳ ሳይፈልግ በሐሰተኛ ወሬ ብቻ የሚበረግግ መሆኑ

፮ኛ/ ሕዝቡ ችግሮቹን ተረድቶ በመግባባት እንዲያስወግዳቸው ታፍኖ መኖሩ ናቸው። እንግዲህ የመሬት ይዞታ ሥርዓታችንን በስም መለወጥ ብቻ ሳይሆን በለውጡ ለመጠቀም የምንችልበት ዕድል ባገኘንበት በአሁኑ ጊዜ ከነዚህ ችግሮች አንዳንዶቹ በመጠኑ የደከሙ ቢመስሉም ገና እንዳሉ ማወቅ

አለብን። ከዚህ በላይ «መሬት ለአራሹ» ሲባል «ጢሰኛው ገበሬ ራሱ ለራሱ የሚሠራበት መሬት ኑሮት ከጢሰኝነት ይውጣ» በሚለው ስሜቱ ሁላችንም መቶ በመቶ ከመስማማት ጋር አንዳንድ የተሳሳቱ ትርጉሞቹን አስተውለን ማረም ከብዙ ጉዳት ያድነናል። ከሁሉ በፊት መሬት የገበሬዎች ብቻ መጠቀሚያ ወይም የግል ርስት አይደለችም። ሰው ብቻ ሳይሆን በመሬት ላይና ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ፍጡር የመሬት ባለቤትነት መብት አለው። የፋብሪካ ሠራተኞች ሐኪሞች መሐንዲሶች ወታደሮች መምህራን አርቲስቶች ተማሮች ካህናት መኃይምናን በጠቅላላው የሰው ዘሮች ሁሉ በመሬት ላይ እየኖሩ በመሬት ላይ ስለሚሠሩ ሲሞቱ እንኳ በመሬት ሰለሚቀበሩ ፍጹም የመሬት ባለቤቶች ናቸው። ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንስሳት አራዊትን አእዋፍና ዕፀትን የመሰሉት ፍጥረቶች ሁሉ የሚገባቸው የመሬት ድርሻ ካላገኙ ያላቸው ዕድል ከመሬት ገጽ መጥፋት ስለሆነ ሰውም ያለነርሱ ሊኖር ስለማይችል መሬት «አራሾች» ወይም «የሰፊው ሕዝብ» የግል ሀብት ብቻ ሳትሆን በላይዋ የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ የጋራ ርስት ናት።

የመሬት ይዞታ ሥርዓት ይለወጥ ስንልም ይህን ሁሉ ጨምረን ማሰብና ላልተረዱት ማስረዳት አለብን።

የአንድን አገር ሕዝብ መሠረታውያን ጥቅሞች ለመጎልመስ ጥረት በሚደረግበት ጊዜ አንዱን ወገን ያለ በቂ ምክንያትና ያለወግ ጎድቶ ሌላውን ወገን ያለወግና ያለ ምክንያት ለመጥቀም ወይም ማንንም ሳይጠቅሙ ሁሉንም ለመጉዳት መታገል ከጤነኞች ጠቅሙ ሁሉንም ለመጉዳት መታገል ከጤነኞች ሰዎች የሚጠበቅ አይደለም።

በራሴ በኩል ይህቺን ትንሽ መጽሐፍ (ፓምፍሌት) ስጽፍ በአንድ የመሬት ይዞት ወይም በጠቅላላው በአንድ ሀብት አፈራርና ይዞታ ትምህርት የሠለጠንሁ ኤክስፐርት ነኝ በማለት አይደለም። ይሁን እንጂ አንድ ኢትዮጵያዊ ስለ ሀገሩ ችግር ከተመራመረ ከአንድ የውጭ ኤክስፐርት የተሻለ ሐሳብ ሊያቀርብ ይችላል ብዬ አምናለሁ።

በተለይ የአንድን አገር ሕዝብ ባህል ማኅበራዊ ኑሮና ፖለቲካ ስለሚመለከት ጉዳይ የተጨበጠ ሐሳብ ለማቅረብ በክፍል የሚሰጥ ትምህርት ብቻ ሳይሆን የባለጉዳይ ሀገር ተወላጅ ጉዳይን በቅርብ ማስተዋልና በጥንቃቄ ማጥናት አስፈላጊ ነው።

ስለዚህ የሀገራችንን ችግሮች ለማስተዋል ብዙ ምክንያቶች ያጋጠሙኝ እንደመሆኑ መጠን ለጀመርነው ለውጣችን የመጀመሪያ ተግባር ሁኖ ስለሚገኘው የመሬት ይዞታ መለወጥ ይረዳል ብዬ ያመንሁበትን ሐሳብ ለመግለጽ ፈለግሁ።

ምንም ውጣ ውረድ ሳይኖር «መሬትን በጠቅላላው መንግሥት በቍጥጥሩ ሥር ማዋል አለበት» የሚሉ ሰዎች አሉ።

ይህ ነገር እንዲህ እንደ አነጋገሩ በቀላሉ ሊፈጽም የሚችል ቢሆን ኑሮ እኔም ይኸን ዘዬ (ስሎጋን) ባስተጋባሁ ነበር። ነገር ግን ይህ ንግግር በአሁኑ ጊዜ በቀጥታ በሥራ ላይ ይዋል ማለት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን እንዲሁም ያለባትን ችግር ባለመገንዘብ ወይም በግዴለሽነት የሚነገር ነው።

በተለይም አሁን በሀገራችን የተጀመረው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ፍጹም ሰላማዊነቱና አስደናቂ ውጤቱ በአንድ ላይ ሲታዩ ታላቅ ተአምር ያለበት ስለሆነ መድኃኒት የሌለው ከባድ ችግር ካላጋጠመን በቀር ይህን ሰላማዊ ለውጥ ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመምራት የሚችሉ ስኅተቶች እንዳይፈጸሙ በጣም መጠንቀቅ አለብን።

ኢትዮጵያ በተባበሩ ልጆችዋ ጥረት ለማንኛውም አገር ጠቃሚ ሁኖ ከተገኘ የሥልጣኔ ደረጃ የማትደርስበት ምክንያት ከቶ አይኖርም።

ይህን ከተፈለገ ግብ ያደርሰናል ብለን የምናምንበትን አንድነት ለማግኘትም አስቀድሞ ሕዝቡን ማሳመን እጅግ አስፈላጊ ነው።

የሀገራችን ሕዝብ አስተዋይና ንቁ መሆኑ ያለጥርጥር የተረጋገጠ ነው። ይሁን እንጂ ካለፈው የኑሮ ሥርዓቱ ጋር በመጠኑም ቢሆን ሊጋጩ የሚችሉ አዳዲስ ሐሳቦችን በግድ ተቀበል ከሚሉት በቅን መፈስ ቢያረጋግጡለት ይበልጥ ከልብ ሊቀበለው ይችላል።

አንድ ኢትዮጵያዊ የግሉ በሆነች ትንሽ ርስቱ ይኮራ ይሆናል። ግን ጉዳዩን ከመንደሩ ራቅ አድርጎ በሚመለከተው ጊዜ ዋናዋና ሰፊዋ ርስቱ ኢትዮጵያ ራሷ እንጂ ያቺ ባንዲት ቀበሌ ያለች ቁራሽ መሬት አለመሆኗን መገንዘብ አይሳነውም። አንድ ኢትዮጵያዊ በጣም ወደ ራቁ ሀገሮች ቀርቶ ቅርብ ጎረቤቶቻችን ወደ ሆኑት ወደ ሱዳን ወደ ኬንያ ወደ ሱማሊያ ቢሔድ

የሚታወቀው በኢትዮጵያዊነቱ እንጂ በአንድ ቀበሌ ባለቺው ትንሽ ርስቱ አይደለም።

ስለዚህ አንድ ሰው ለሀገሩ ጠቅላላ ደኅንነት ራሱ ሳይነካ የሚቀርብለትን ጠቃሚና አዳዲስ ሐሳብ ሁሉ የልማድ ሰንሰለቱን በጣጥሶ እየጣለ ሊቀበል ይገባዋል።

አዲሷ ኢትዮጵያ የምትራመድበት ቅን ጐዳና በጣት የሚቈጠሩ ሰዎችን የሀብት ሥልጣን በጠቅላላው የሁሉ ነገር ጌቶች አድርጎ አብዛኛውን ሕዝቧን የውርደትና የችግር ሁሉ ተሸካሚ የሚያደርግ ሳይሆን ሀገሪቱ ለሚኖራት ለማንኛውም ነገር ጠቅላላው ሕዝብ ሙሉ ተሳታፊነት እንዲኖረው የሚያደርግ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሀገሩ ለምትጠቀምበትም ሆነ ለምትጎዳበት ነገር ሙሉ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አምኖ ለግል ቤቱ መሟላት የሚያደርገውን ልባዊ ጥረት ለናት ሀገሩ ደኅንነትም ማድረግ ብሔራዊ ተግባሩ ነው። በአሁኑ ጊዜ የመሬት ይዞታ ይለወጥ ሲባልም እያንዳንዱን ሰው ከርስቱ ነቅሎ ለተወሰኑ ሰዎች ጢሰኛና ገባር ለማድረግ ሳይሆን ኢትዮጵያ በሙሉ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የጋራ ርስት ሁና በኅብረትና በአዲስ ዘዴ ሥርተን ሰብአዊ ክብራችንን ሳይቀር አዋርዶት ከሚገኘው የመከራ ኑሯችን ለመላቀቅ ነው።

ስለዚህ ይህን ለውጥ ማንኛችንም ወገኖች በጥርጣሬ ሳናይ ልንተባበርበት ይገባል።

ለለውጡ መግባባት እንጂ ኃይል ብቻ አይጠቅምም።

ኢትዮጵያ ሕዝብና ወታደር ተባብሮና ተፋቅሮ ከተራመደ እጅግ አስፈላጊና ተቀዳሚ ስለሆነው የመሬት ይዞታ ለውጥም በሰላም ሊፈጽመው የማይችል ተግባር እንደማያጋጥመው ባለፉት ጥቂት ወራት የተፈጸሙት ተአምራቶች አረጋግጠውናል። ኃይላችንና ልባችን ተከፋፍሎ ቢሆን ኑሮ እነዚያ እንደዘበት ከአናታችን ወርደው የተንኮታኮቱ ኃይሎቹ ስንት ጉድ ሊሠሩብን ይችሉ እንደነበረ መዘንጋት የለብንም።

አሁንም ኅብረታችንና ሰላማችን ይበልጥ አስፈላጊዎቻችን ናቸው ስል ካሁን በፊትም በጋዜጣ ደጋግሜ ያቀረብኳቸውን ምክንያቶች ላቀርብ ነው።

፩ኛ/ ኢትዮጵያ ውስጥ ወታደራዊው ክፍል ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ በሥልጣኔ ወደ ኋላ የቀሩ የሚባሉት ቀርቶ ራሳቸው የተራቀቁ የጦር መሣሪያዎች የሚጠሩ ሕዝቦች እንኳ ያደርጉታል ተብሎ በማይጠረጠር መጠን በጦር መሣሪያ የደረጀ የወታደርነት ወኔ የተጫነው በመሆኑ ለኛ ሀገር የርስ በርስ ጦርነት ማለት በሚሊዮን በሚቈጠሩ ነፍሶች ላይ የአረመኔ የሞት ፍርድ ያለ ምክንያት ማስተላለፍ ነው።

፪ኛ/ ማንኛውንም የሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በጦር ኃይላችን ጉልበት ብቻ ፀጥ እናድርግ ብንል

ሀ/ የሀገሪቱን አንድነትና ወሰኖቿን በማስከበር ግዴታው ላይ የሚገኝ የጦር ኃይላችንን ወደ ማያስፈልግ ከወገን ጋር የመፋጀት ግዴታ አስገብቶ ሀገራችንን ከፍጹም ጥፋት ላይ መጣል

ለ/ የወደቀው መንግሥት ርዝራዦች በምክንያት እንዲያንሠራሩ ማድረግ ይሆናል።

፫ኛ/ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሀገር የርስ በርስ ግጭት መቀስቀስ ማለት የውጭ ኃያላንን «ኑ ግቡና ቀልዱብን» ብሎ በቀጥታ መጋበዝ ነው።

፬ኛ/ በግል ስሜታችን ኃይል በመገደድ የመጣውን ይምጣ ብለን አንዳንድ ሀገራቸውን በሚገባ የሚያውቁት ሰዎች እንደሚሉት በኃይል ብቻ ይሠራ ብንል

ሀ/ የሚባክነው ገንዘብና የሰው ጉልበት በሀገሪቱ የደከመ ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ውድቀት

ለ/ ለረጅም ጊዜ ሊደርስ የሚችለው የሰላምና ፀጥታ መታጣት

ሐ/ በመካከላችን ሊፈጠርና የረጅም ዘመን የኑሮ ጠንቅ ሆኖ ሊቆይ የሚችለው ጥላቻና አለመተማመን ይህን ተአምራዊ ለውጣችንን ወዳልተጠበቀ የስኅተት ፍጻሜ ሊመራው ይችላል።

እንግዲህ ከዚህ ላይ ነው «ያገሩን ስርዶ ባገሩ በሬ» የሚባለውን የምሳሌ አነጋገር ልንጠቀም የሚገባው። በደቡብ ኢትዮጵያ ከወሰን አለፍ ያለ መሬት የያዙ ግን ሌላ ጉድለት የሌለባቸው

# ኢትዮጵያውያን ድርሻ።

ታላላቅ መሬት ዘራፊዎች ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በቍጥር ሲነጻጸሩ ጥቂቶች ከመሆናቸው በላይ እንደ ወደቁት መሪዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብና አፈሩ የከዳቸው በመሆናቸው ቢወዱም ቢጠሉ መሬታቸው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደ መንግሥት ተዛውሮ መንግሥት ለሌላ ብሔራዊ ተግባር የሚያውለው በመንግሥት እጅ ሲቀር የቀረው መሬት ለሌላቸው ገበሬዎች እንደየ አስፈላጊነቱ መሰጠቱ እንደማይቀር ይጠራጠራሉ ተብሎ የማይታሰብ ነገር ነው።

ነገር ግን እንደዚያም ባይበዛ ከሚያስፈልጋችሁ በላይ መሬት የያዛችሁ ሁሉ ችግሩ በጊዜውና በተራው ወደናንተም ዓይኑን አፍጥጦ እስከ ሚመጣ መጠበቅ አይለባችሁም።

በአሁኑ ጊዜ የታወቁት በቃኝ - አይሌዎቻችን ሁሉ «እኔን ያየህ ተቀጣ» እያሉ ወደፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገባቸው በላይ እየዘረፉ ወገኖቻቸውን መድረሻ ለሚያሳጡ ሰዎች ቦታ እንደማይኖራቸው መማሪያ ሁነዋል። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከቅርብ ባለሟሎቻቸው በላይ በሥልጣኑ በሀብቱ በትውልዱና በጉልበቱ የተመካ ማንም ይደፍረናል ብሎም ያልተጠራጠረ ኢትዮጵያዊ አልነበረም።

ነገር ግን የአብዛኛውን ሕዝብ ምኞትና ፍላጎት በንቀት አልፎ ጥቅሙን ዘርፎ መብቱን ገፍፎ ከጥጉ ባሉ ጥቂት የጥቅም መሰሎቹ ብቻ ተማምኖ የሚኖር ወገን ሁሉ ያ የተናቀ ብዙ ሕዝብ በኀበረት በተነሣ ጊዜ መውጫ ቀዳዳ ስለሚገኝ የኛም ናቂዎች በሚገባቸው ጉድ ላይ ወደቁ።

በነሱ የማይማሩ ደግሞ ምናልባት ከዚህ በከፋ ጉድ ላይ ሊወድቁ ይችላሉ።

አባቶቻችን ሆይ!

ከአሁም ቢሆን የራሳችሁ ልጆች ሳይቀሩ ተነሥተውባችኋል። «መሬት ለአራሹ» እያሉ ከሚዘምሩት አብዛኛዎቹ የተሻለ የመማር ዕድል ያገኙት የናንተው ዓቅም ያላችሁ ሰዎች ልጆች ናቸው። የምስኪኑ ጢሰኞችሁ ልጅማ

የተማረና ባለብዙ ርስት ለሚሆነው ልጃችሁ እሱም በተራው ጢሰኛ ለመሆን ከተወለደበት መንደር ሳይወጣና ፊደል የመቍጠር ዕድል ሳያገኝ ቆይቷል።

በጊዜው የሚመጣ ኃይልን ጊዜው ባለፈበት ድርቅና መቋቋም አይቻልም። በብዙ ሀገሮች የመሬትን ይዞታ ሥርዓት አናስለውጥም ብለው በተቃወሙ ሰዎች ላይ የተፈጸመ አሳዛኝ ነገር ሞልቷል። እኛ ግን ለውጣችን የመጣልን በሰላምና በመግባባት ስለሆነ በዚህ በኩል የሚፈልገውን ለውጥም በሰላም እንደምናከናውነው አይጠረጠርም። ይህንንም ስናደርግ ማንም የመኖር መብቱን ሳያጣ ጠቅላላው ሕዝብና ተተኪ ትውልዶቻችን የሚጠቅሙበትን መንገድ በሰላም ለመክፈት እንችላለን።

ስለዚህ ቀላሉ ነገር ከባድ መስሏችሁ ቀድሞ ለመገኘት ስትቸገሩ የማይቀር ከባድ ችግር ደርሶ እንዳይዛችሁ ለሰላማዊ ለውጣችሁ ፍጹም ተባባሪ ብትሆኑ ከፍተኛ የሀገር ፍቅር የሥልጣኔ የጨዋነት የብልህነትና የሰላም መንፈስ ከሀገራችን ሳይጠፋ ሀገራችሁ እንድትለወጥ አደረጋችሁ ማለት ነው።

# የጢሰኞች ድርሻ

ጢሰኞች ሁነው የኖሩ ኢትዮጵያውያን ለወገኖቻቸው ዐውቀው ባዳ መሆን እንደ ሌለባቸው ሊያስተውሉ ይገባል። በአሁኑ ጊዜ ለነሱ መሬት ለመስጠትና እነሱን ብቻ ለመርዳት ሲባል ባለርስት ነኝ የሚለውን ሁሉ ወሰን ሳይለዩ ትነቀላለህ ቢሉት ምን ዓይነት ችግር እንደሚፈጠርና በዚህም ሳቢያ የነሱም ሰላም በቂ ዋስትና እንደማይኖረው ማወቅ አይሳናቸውም። ኢትዮጵያ ለሁከተኛ ለውጥ የምትመች አገር አይደለችም። ምክንቱም ሁከት ብንፈጥር ተመልሶ የሚያጠፋና ራሳችንን ነው። የጦር ኃይላችን በንቃትና በጥንቃቄ ሊያስወግዳቸው የተጠመደባቸው የመሬት ይዞታና ሥርዓት ከመለወጥ ጀምሮ ብዙ የሀገር ውስጥና የወሰን ችግሮች ስላሉበት ተጨማሪ ችግሮች መፍጠር ሀገርን በቀጥታ መበደል ነው።

ስለዚህ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜና አካባቢ ሁሉ መንግሥት ተስማሚ ቦታ እያዘጋጀ በተሻለ ዘዴ ሊያሰፍራችሁና ሊረዳችሁ ሲፈልግ መሬት ከነእገሌ ቀምታችሁ ካልሰጣችሁን ብሎ ማስቸገር የለውጡን እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን የራሳችሁን ነጻነት ጭምር መቃወም ይሆናል።

በአካባቢያችሁ ታውቋቸው ከነበሩ ጎረቤቶቻችሁ ጋር ካንድ የራሳችሁ ካልነበረና የሰው በታች ሁናችሁ ከቆያችሁበት ቦታ ተነሥታችሁ በዘመናዊ መልክ እየሠራችሁ ወደ ምትኖሩበት የራሳችሁ ቦታ ስትዛወሩ የእምትጎዱበት እናንተ አይደላችሁም። እናንተ ከነበራችሁበት ቦታ በመነሣታችሁ የሚጎዱት ሰዎች የምትለቋቸው መሬቶች ባለቤቶች የነበሩት ናቸው።

ምክንያቱም

፩ኛ/ እናንተ ስትለቁት ባዶ መሬታቸው ምንም ጥቅም ሊሰጣቸው ስለማይችል የባለ መሬትነት ትርፋቸው ድካም ብቻ ይሆናል።

፪ኛ/ የማይጠቀሙበትን መሬት ለስም ብቻ ይዘው ከባድ ግብር መገፍገፍ ስላማይፈልጉ ለችግር ያቦዘኑትን መሬት በፈቃዳቸው ለመንግሥት ያስረክባሉ።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ የናንተ ተባባሪነት ለራሳችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው ሕዝብ ሰላማዊ ርምጃ ከፍተኛ ድርሻ አበረከተ ማለት ነው።

የሀገራችንን ርምጃ እንቅፋቶች በያለንበት በያቅጣጫው በየችሎታችን በአንድነት ለመዋጋት እንሰለፍ። ኢትዮጵያ በማያዋጣ የተሳሳተ መንገድ እየተመሩ ሁከትን ለማስፋፋት ከሚቀባጥሩ ሰዎች ይልቅ ባላቸው ችሎታ በያሉበት በጎ ፈቃድና ኅብረትን የሚደግፉ ልጆችዋን ትፈልጋለችና እንተባበር።

# የሰሜናዊ ሕዝብ ድርሻ

ባሕልና ወግን ማክበር ሃይማኖትን ማፅናት ሀገርን መውደድ ከፍተኛ ሰብአዊ ተግባሮች ናቸው። ነገር ግን አእምሮን አጥብቦ ሀገር በተወለዱበት መንደር መከለል እግዚአብሔር ያላዘዘንን አንዳንድ መጥፎ ልማዶች በሃይማኖት ስም እያስጠጉ ራስን መበደልና ለሀገር ዕድገት ዕንቅፋት መሆን እጅግ አሳፋሪ ነገሮች ናቸው።

በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች ከዓመት ዓመት የሰው ቊጥር እየጨመረ መሬት ከኖረበት ሁኔታ ምንም ስላልጨመረ ለኗሪዎች እየጠበበ ሲሔድ ካንድ አገር ከፍተኛ የሀብት ምንጮች አንዱ የሆነው ድነ ቀርቶ ለማገዶ የሚሆን

ቁጥቋጦ እየጠፋ ሲሔድ በየዓመቱ አፈሩ እየታጠበና ምድሩ እየሳሳ ሲሔድ የግጦሽ ቦታዎች እየጠበቡና እየተራቆቱ የከብቶች ቊጥርና ባለውም ቊጥር የሚሰጡት ጥቅም እየቅነሰ ሲሔድ ሌላም ይህን የመሰለ ችግር ተደራርቦ ሲመጣበት እያየ ራሱንና ሀገሩን ለማዳን እግዜር ካወረደለት ኃይል ጋር የማይተባበር ሰው ከጥፋት ወሀ በፊት ኖኅ መርከብ ሲሠራ እየተዘባበቱ ቆይተው እስኪ ጠፉ ድረስ «አስረሽ ምቺው» አሉ ከሚባሉት የጥንት ሰዎች ጋር ሊመሳሰል የሚገባው ነው።

መቼም ዋና ዋናውን የሀገሪቱን ችግር ሁሉም በየቤቱ ሁኖ እንዳይመለከተው የየግል ችግሩ ክብደት ጋርዶት ነው እንጂ ኢትዮጵያ አሁን ያለቺው ታላቅ መሥዋዕትነት በምትጠይቅበት ጊዜ ላይ ነው።

ተርባለች እናብላት።

ተጠምታለች እናጠጣት።

ታርዛለች እናልብሳት።

ታሥራለች እንፍታት።

ታማለች እናስታማት።

በገዛ ቤቷ ዕንግዳ ሁናለች እናስተናግዳት።

፪ኛ/ የማይጠቀሙበትን መሬት ለስም ብቻ ይዘው ከባድ ግብር መገፍገፍ ስለማይፈልጉ ለችግር ያቦዘኑትን መሬት በፈቃዳቸው ለመንግሥት ያስረክባሉ።

ይህም ማለት የኛ የኑሮ ሁኔታ ከእነዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጡ ከባድ ችግሮች አድርጎ የገለጻቸው ችግሮች ሁሉ የሰፈኑበት ስለሆነ ራሳችን ለራሳችን በደጎንነት እንሥራ ማለት ነው።

በእውነት ከተሔደ ከኛ ይበልጥ የሚያሳዝኑ የተሠቃዩ የሰው ዘሮች የት ይገኛሉ? ምናልባት በጥቂት አገሮች ይገኙ ይሆናል። አንደኛ በመከራው የሚኮራ ሕዝብ ግን በየትም ዓለም እንደሌለ አያጠራጥርም።

ኧረ እባካችሁ እንንቃ! አባቶቻችን ከውጭ ወራሪዎች ጠብቀው ያቆይዋትን ሀገር ከነዚያ ጠላቶች ከሚከፉ ጠላቶች ለማዳን እንሰለፍ!

አሁን ወደ ታላቅ ጦርነት ገብተናል። በችግር በበሽታ በድንቁርና በጭቆና ተከበን መኖራችን አንገፍግፎን በነዚህ ጠላቶቻችን ላይ ድል ለማግኘት ቆርጠን ተነሥተናል። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ደኅንነት የሚመጣውን እውነተኛ ለውጥ ባጉል ግትርነት ለማበላሸት መሞከር አገርን ማጥፋት መሆኑን አንዘንጋ።

# አቤ ጉበኛ።

## የችግሩ ምክንያቶች

የአንድ አገር ሕዝብ ጠቅላላ የኑሮ አቋም ለመለወጥ በሚፈልግበት ጊዜ የሀገሩን ችግሮችና ችግሮቹን ለማስወገድ የሚቻልባቸውን ዘዴዎች ግልጽ በሆነ መንገድ ለመመልከት መቻል የመጀመሪያ ተግባር ነው። ከዚያ ቀጥሎ የሚያስፈልገው ነገር ደግሞ ለለውጡ የሚጠቅሙ ተግባሮችን ቅደም ተከተል ተረድቶ በኅብረትና በፅኑዕ በጎ ፈቃድ ለሥራ መራመድ ነው።

ስለ ሀገራችን ፈጣን የኢኮኖሚ ለውጥ በምናስብበት ጊዜም የመሬት ይዞታችን አቋም በተቀዳሚነት በአእምሮአችን የሚደቀን ከፍተኛ ችግራችን ሁኖ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ንግግር ሲደረግበት ቆይቷል። ይህ የሆነበት ምክንያትም የመሬት ይዞታችን ሥርዓት ዝብርቅርቅነት ብቻ ሳይሆን ሀገራችን በልማት በኋላ መቅረቷና የተፈጥሮ ጸጋዋም ለርሻ ሥራ ተቀዳሚነት እንድንሰጥ ስለሚያስገድዱን ነው።

በሀገራችን የመሬት ይዞታ ሥርዓት ውስጥ ብዙ ጥቃቅን ልዩነቶች በየክፍለ ሀገሩ ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ጥቃቅን ልዩነቶች ብዙ የጎሉ ስላይደሉ ብዙ ላያስቡ ይችላሉ።

ነገር ግን በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍሎችና በደቡባዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች ያሉት የመሬት ሥሪቶች እጅግ የተለያዩ ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ አጠራራችንና እኔም እሱን ተከትዬ እንደጠራሁት ሰሜናዊ ኢትዮጵያ የሚባለው አማርኛና ተናጋሪ የሆኑት ኢትዮጵያውያን ርስት አድርገው እስከ ዛሬ የኖሩበት ክፍለ - ኢትዮጵያ ነው።

በዚህ ክፍል በሚገኙ የተለያዩ አውራጃዎች የመሬት ሥሪት ውስጥ እጅግ ጥቃቅን የሆኑ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ግን የመሬቱን ይዞታ በፍጹም አንድ የሚያደርጉት ሁለት ታላላቅ ምክንያቶች አሉ። እነሱም፡-

በዚህ ክፍል በሚገኙ የተለያዩ አውራጃዎች የመሬት ሥሪት ውስጥ እጅግ ጥቃቅን የሆኑ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ግን የመሬቱን ይዞታ በፍጹም አንድ የሚያደጉት ሁለት ታላላቅ ምክንያቶች አሉ። እነሱም፡-

፩ኛ/ በነዚያ አውራጃዎች መሬት ማለት የማይሸጥ የማይለወጥ የማይቀማ የተወላጆቹ የጋራ ርስትና ሀብት ነው።

፪ኛ/ አንድ ሰው የነዚያ አውራጃዎች ተወላጅ ከሆነ ከተወላጆቹ ጋር የሚካፈለው የጋራ የሆነ የትውልድ ርስት አለው። ስለዚህ ለያንዳንዱ ሰው ያለው ዕድል አሳርሶ ከመብላት ይልቅ አርሶ መብላት ሲሆን ከትውልድ ቦታው ካልወጣ በቀር ማንም ጢሰኛና ገባር ሊያደርገው አይችልም። የዕለት ራት የሚያሳጡት ችግሮች ቢኖሩበት

ሀ/ እንደ በረድ ድርቅ ጎርፍ አንበጣና እነሱን የመሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች

ለ/ የአሠራሩ ዘዴዎች ደካማነት ማለት የርሻውና የእርባታው ዘዴ ጨርሶ ያልተሻአለና ትርፉ ከድካሙ ጋር በምንም የማይመጣጠን መሆኑ

ሐ/ የአስተዳደር የፍርድና የፀጥታ አለመሟላትና የሙግት ብዛት

መ/ የበዓላት ብዛት

ሠ/ ሥራን መናቅና ስንፍና ናቸው።

ከነዚህ ነገሮች በአንዱ ያልተጎዳ ከሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች አንዱ የዘር የትውልድ ቦታው

የሆነ ኢትዮጵያዊ ይነስም ይብዛ ሠርቶ የሚኖርበት የግሌ የሚለው የትውልድ መሬት አለው።

ይህም በመሆኑ የሰሜናዊ ኢትዮጵያ መሬት ያው ቋሚ የሆነ የጠቅላላው ተወላጅ የጋራ ርስት ሁኖ ኑሯል ለማለት ተችሏል። ይሁን እንጂ በነዚያ ክፍሎች በቍጥራቸው በጣም አነስተኛ በሆኑት የጅ ባለሙያዎችና በሌሎች በቍጥር አነስተኛ በሆኑ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች ላይ የቆየውን ክፉ

ልማድ በመከተል ባለርስት የሚባለውን ስም የመከልከል ልማድ ስላለ በትምህርትና በመግባባት ማስወገድ እጅግ ያስፈልጋል።

፪ኛ የደቡባዊው ኢትዮጵያ ክፍል።

በልማዳዊው አነጋገራችን ደቡባዊው የኢትዮጵያ የምንለው ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ በሕዝብ ብዛት ታላላቅና ታናናሽ የሆኑ ልዩ ልዩ ነገዶች ያሏቸው ኢትዮጵያውያን በበዛት የሚኖሩባቸውን የኢትዮጵያ ክፍሎች ነው። የዚህ ክፍሎች መሬት ባለፈው የኑሮ ሥርዓት እንደታየው የተወላጆችም ሆነ ከሌሎች ክፍሎች የመጡ ተራ ኢትዮጵያውያን ቋሚ ርስት አልነበረም።

ይህም በመሆኑ ቀደም ብሎ ከተባለውና ከተራቆተው አብዛኛው የሰሜናዊ ኢትዮጵያ መሬት ይልቅ ለምና ድንግል የሆነው የኢትዮጵያ ክፍል በብዛት የሚከተሉት ወገኖች ተቀራምተዉት ብዙው ደሀ ተወላጅ ከገባርነት በማይሻል ጢሰኝነት ሲቆራመድበት በበረታውም ክፍል በዘላንነት ሲንከራተትበት ኑሯል።

፩ኛ/ ባስፈለገበት ጊዜ ሁሉ ለንጉሥና ለንግሥት ለልዑላን ልዕልታት ለክቡራን መኳንንትና ወይዛዝርት ለታላላቅ የጦር አለቆችና ለተወደዱ ደጀጠኝዎች ለመታደል እንዲመች የመንግሥትነት ጠባይ ሳይኖረው መንግሥት በመባል ተቋቁሞ በኖረው የቅሚያና የሥርዓት ድርጅት ስም ተይዞ የቆየ ብዙ መሬት አለ።

፪ኛ/ ንጉሡ ለራሳቸው ለባለቤታቸው ለልጆቻቸው ለልጅ ልጆቻቸው እንዲሁም በቅርባቸው ሁነው በዝርፊያ ለተባበሯቸው መሰሎቻቸው ሁሉ ዓይናቸው በቻለ ቃላቸው በተናገረ መጠን እየመረጠ ያከፋፈሉት ብዙ መሬት አለ።

፫ኛ/ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ አብሯቸው ለደከመ ወታደራቸው ሁሉ በደመወዝ መልክ ይሰጡት የነበረው ሀብት ርስት ስለነበር ለራሶችና ለደጃዝማቾች ከነተከታዮቻቸው የስጡትን የጋራ ርስት ጮሌዎች መሳፍንትና መኳንንት ለየራሳቸው እየጠቀለሉ ወስደውት ዛሬ በልጆቻቸው ወይም በልጅ ልጆቻቸው ስም የሚገኝ ብዙ መሬት አለ።

፬ኛ/ ባለፈው መንግሥት በከፍተኛም ይሁን በዝቅተኛ ሥልጣን እየተሾሙ ወደ ነዚያ ክፍሎች ሒደው በሥልጣን በተደገፉ ልዩ ልዩ ተንኮሎች ባለርስቶችን እየቀሙ የያዙት መሬት አለ።

፭ኛ/ ፍጹም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ አራጣ እያበደሩና ደሀውን ገበሬ በዘዴ አሳስተው በኋላ እያስጨነቁ መሬት ሲዘርፉ የኖሩ አራጣ አበዳሪዎች የያዙት መሬት አለ።

፮ኛ/ ተወላጅነታቸው በዚያው ክፍል ሁኖ እንደባላባትነት ባሉ ከልጅ ወደ ልጅ በሚተላለፉ የዘር ሹመቶችና የተለዩ ተከባሪነቶች ስም በአንዳንድ ሰዎች በብዛት የተያዘ መሬት አለ።

የደቡባዊ ኢትዮጵያ መሬት የሚሸጥና የሚለውጥ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ የሚቀማ ሁኖ ኖረ ለማለት ይቻላል። ከዚህም በላይ እንደ ሰሜናዊ ክፍል የግብርና ሥራ ሁሉ ምንም ባልተሻሻለና ውጤት ከድካሙ ጋር ፈጽሞ በማይመጣጠን ደካማ የርሻ ዘዴ የሚተዳደረው አብዛኛው የደቡባዊ ኢትዮጵያ ገበሬ ያቺውን ያፈራትን ትንሽ የላብ ፍሬ ታላላቅ የመንግሥት ሥራና ሥልጣን ከነ ከፍተኛ ደምወዙ ለያዙ ከፍተኛ የኪራይ ገቢ ያላቸው የከተማ ቤቶችና ሰፋፊ ርስት የተደበቀ የሽርክና ንግድ ሕግ ጣልቃ ሊገባበት ያልቻለ ጉቦ ከዚህም በላይ የጠገበውን ሆድ ጨርሶ በቁንጣን ለመተርተር በንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ትእዛዝ ከመንግሥት ግምጃ ቤት የሚሰጥ ሰፊ ጉርሻ ላናጠጣቸው ባለጊዜዎችና ያን የዝርፊያ ዘመን እንደ ከፍተኛ ዕድል በመቍጠር ደሀውን ሕዝብ ሲዘርፉ ለኖሩ ግብረ አበሮቻቸው ሲገብር ቆይቷል።

ይህም በመሆኑ የደቡባዊ ኢትዮጵያ የመሬት ሥሪት የአብዛኛውን ሕዝብና የመንግሥቱን ጥቅም ምን ያህል እንደጎዳው እንመልከት።

፩ኛ/ ለፍቶ ለፍቶ ከልፋትም ልፋት ባልተሻሻለ የሥራ ዘዴ ደክሞ የፈራውን የግብርና ውጤት ለጠገበ ባላተኛ የማስረከብ ግዴታ ስለተጫነበት የያንዳንዱ ጢሰኛ ገበሬ የሥራ ፍላጎት ከዓመት ዓመት እየደከመ በመሔዱ የብዙዎች የነዚያ ክፍለ ሀገሮች የርሻ ሥራ ውጤት ከለምለምነታቸውና ከድንግልነታቸው ጋር ፈጽሞ የማይመጣጠን ሁኖ ይታያል። ባንዳንድ ክፍል ቡና በሌሎችም ብዙ ከብት ባይኖርማ እነዚያ ክፍሎች የረኀብ ክፍሎች በመባል በታወቁ ነበር።

፪ኛ/ ሰፋፊውንና በይበልጥ ፍሬያማ ሊሆን የሚችለውን መሬት በየክፍሉ የያዙት መሬት ዘራፊዎች

ሀ/ ብዙውን በስማቸው ተከብሮ በጠፍነት እንዲኖር በማድረግ

ለ/ በለሙም በጠፉም ለመንግሥት የሚገባውን ግብር ባለመክፈል ሀገሪቱን አደህይተዋል።

፫ኛ ሌላው የደቡባዊ ክፍል አቋም።

ምንም እንኳ የደቡባዊው ኢትዮጵያ ክፍል መሬት ከፍ ብዬ እንደገለጽሁት ሲሸጥ ሲለወጥና ሲቀማ የኖረ ቢሆን በተለያዩ ምክንያቶች በአንዳንድ ሰዎች እጅ በግል ርስትነት የተያዘ መሬት ይገኛል። ይኸውም እንደሚከተለው ነው።

፩ኛ/ የዘር ርስታቸው ሳይሸጥ ሳይለወጥ ወይም ሳይቀማ የተላለፈላቸው አንዳንድ የክፍሉ ተወላጆች የያዙት መሬት

፪ኛ/ አያቶቻቸው ወይም ቅድመ አያቶቻቸው ከማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል መጥተው በወታደርነት ላበረከቱት አገልግሎት በጊዜው እንደ ደመወዝ ሁኖ የተሰጣቸውን ርስት ወርሰው የሚገኙ ነፍጠኞች ወይም የነፍጠኞች ልጆች የያዙት መሬት (ከዚያ አልፈው ከዘራፊዎች ጋር በመተባበር የያዙም አልፎ አልፎ ይኖሩ ይሆናል።)

፫ኛ/ ከሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች

ሀ/ በአንዳንዶቹ መሬት ጨርሶ ተበልቶ ደኑ ተራቁቶ አፈሩ ታጥቦ ዝናሙ

ተቀንሶ ወይም ጭራሽ ጠፍቶ ለግብርና ሥራ ፈስሞ ባለመመቸቱ

ለ/ በሌሎች ክፍሎች ሕዝቡ እየበዛ መሬት እየጠበበ በመሔዱ ወይም በሌላ ችግር

ተገደው ከሰሜናዊው የኢትዮጵያ ክፍል ወደ ደቡባዊ እየሔዱ በገንዘብ በመግዛት የያዙት መሬት አለ።

፪ኛ ክፍል ስለ ለውጡ።

በዓይኔ ያየሁትንና በጆሮዬ የሰማሁትን መረጃ ድጋፍ በማድረግ እስካሁን የቆየ የመሬት ሥሪታችንን የተለያየ አቋም ከሞላ ጎደል የገለጽሁ ይመለኛል።

የሚቀጥለው ጥያቄ መንግሥት የመሬት ይዞታን አቋም በፍጹም ለውጦ በሙሉ ተመሳሳይ የሆነ ዘመናዊ መንገድ ለማስያዝ ምን ማድረግ ይገባዋል? የሚል ይሆናል።

በመግቢያው እንደገለጽሁት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በሚገባ የሚያውቁ አሁን በመካሔድ ላይ ያለው ከፍተኛ የለውጥ እንቅስቃሴ ፍጹም ሰላማዊና ውጤቶቹ ያማሩ የሆነበትን ምሥጢርም ያልተረዱ ደመፍሎች ባጭሩ ሊሰጡት የሚችሉ አንድ መልስ አለ። እሱም መንግሥት አንድ አዋጅ አርቅቆ «ከዛሬ ጀምሮ የኢትዮጵያን መሬት በሙሉ መንግሥት ወርሶታል። መንግሥት እንዳስፈላጊነቱ እያየ ለዕለት ሥርቶ ማደሪያ ከሚሰጠው በስተቀር ባለርስት የሚባል ሰው አይኖርም» ይበል የሚል ነው። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ያለ አዋጅ ይነገር ማለት በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች የርስ በርስ ጦርነት አውጆ የተጀመረውን ሰላማዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱ ን ሕልውና እንደማጥፋት የሚቈጠር ነው።

ይህንንም ስል ከሀገራችን ጠቅላላ ሁኔታና ከአካባቢያችን ሳይጋጭ ሰላማዊ የለውጥ እንቅስቃሴያችንን ዓላማም ሳያበላሽ ከሚፈልገው ግብ የሚያደርሰን ቀላልና ሰላማዊ መንገድ ልንመርጥ ይገባናል ለማለት እንጂ የመሬት ይዞታችን ሊለወጥ አይችልም ለማለት አለመሆኑን ከዚህ ላይ እምገለጽ ሰዎችን የኔ ሐሳብ አይገባችሁም ብዬ እንደሰደብሁ እቈጥረዋለሁ። ምክንያቱም የምጽፈው እጅግ አስፈላጊና ተቀዳሚ ስለሆነው የመሬት ይዞታ ለውጥ ነውና!

በመጀመሪያ ደረጃ።

፩ኛ ክፍል።

፩ኛ/ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት ረጂም ዘመናት ስለመንግሥት የነበረው አስተሳሰብ ፈጽሞ መለወጥ አለበት።

ሀ/ የወደፊቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ወጥተው በሕዝቡ የወለከሉ የሕዝብ አገልጋዮች የሚያቋቁሙት ለመላው

ሕዝብ ሰላምና ብልጽግና የሚሠራ ሕዝባዊ ማኅበር መሆኑን መላው ሕዝብ እንዲረዳው ማድረግ

ለ/ ዘራችን ከዘራችን ደማችን ከደማችሁ ይበልጣል ብለው የሚያምኑ ጥቂት ግብዞች ለግል ጥቅማቸው አቋቁመው ሕዝቡን ረግጠውና አደንቁረው ይገዙበት ሀብቱን ይበዘብዙበት የነበረው ስመ - መንግሥት በወንጀል ማኅበር እንጂ እውነተኛ መንግሥት ያልነበረ መሆኑን ማስረዳት

ሐ/ በአዲሱ ሥርዓት «መንግሥት» ቢሉ «ሕዝብ» ቢሉ «መንግሥት» እንጂ የተለያዩ አካሎች አለመሆናቸውን ሕዝብ ዐውቆ የሕዝቡንና የመንግሥቱን አንድ አካልነት የሚያረጋግጡ ተግባሮችን ማቀላጠፍ ማለት በምንም ዓይነት የመንግሥት ሥራ ተልከው አሮጌውን ልማድና አስተሳሰብ እስካሁን ሳይለቁ በሕዝቡ መካከል የሚገኙትን ሹማምንት በሙሉ ከያሉበት በቅድሚያ አንሥቶ ሕዝቡ አዲስ ሥርዓትና አዲስ ዓለም መጀመሩን በተግባር የሚያረጋግጡለት ቅኖች ትጉሆችና ንቁዎች ኃላፊዎችን መላክ እጅግ ይጠቅመናል።

፪ኛ/ በሰሜናዊ ኢትዮጵያና በደቡባዊ ኢትዮጵያ መካከል ብቻ ሳይሆን በዚያው በደቡባዊ ክፍል እጅግ የተራራቁ የመሬት ይዞታ ልዩነቶች መኖራቸውን የዚያው ክፍል ሕዝብ በሚገባ እንዲረዳና ለውጡን በቅን መንፈስ እንዲመለከት ማስቻል እጅግ ያስፈልጋል።

ሀ/ የታላላቅ መሬት ዘራፊዎች ዘሮች ወገን ለማብዛትና ቢቻል ብጥብጥ ፈጥሮ የወደቀው የቅሚያ ሥርዓታቸው ተመልሶ እንዲያንሠራራ ለማድረግ ርስት ያለው ሰው ሁሉ ተነቅሎ መሬት ለሰፈረበት ጢሰኛ ብቻ ሊሰጥ ነው እያሉ የሚነዙትን ወሬ መውረሱ የሚመለከት እነሱን ዘራፊዎችን ብቻ መሆኑን ገልጦ ማጋለጥ

ለ/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሩ የራሱን ድርሻ መሬት የማግኘትና በዚያው ላይ ዓቅሙ እስከቻለ የመሥራት መብት ስላለው በውርስም ሆነ በግዢ የተወሰነ መሬት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ በታላላቅ መሬት ዘራፊዎች ላይ ሊፈጸም የሚችለው ውርስ በአሁኑ ጊዜ ፈጽሞ የማይመለከታቸው መሆኑን ዐውቀው በለውጡ ላይ ጥርጣሬ እንዳይኖራቸው ማስረዳት

፫ኛ አሁን በጢሰኝነት የሚገኙት ገበሬዎች ሁሉ ሊደረግላቸው የታቀደውን ነገር በትክክል እንዲረዱት ማድረግ ያስፈልጋል።

ሀ/ መንግሥት የሚሰፍሩበት የራሳቸው መሬት እንደሚያዘጋጅላቸውና ለመቋቋም በሚገባ እንደሚረዳቸው ተገንዝበው አስተሳሰባቸውን ብቻ ሳይሆን የቆዩበትን ቦታ መለወጥ እንዳያስቸግራቸው ማሳመን

ለ/ መንግሥት የሚወርሰው ታላላቅ ዘራፊዎች ያለወግና ያለልክ የዘረፉትን መሬት እንጂ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከልክ ሳያልፍ የያዘውን መጠነኛ መሬት ሁሉ ስላልሆነ ሰፍሬበት ከቆየሁ የማንንም መሬት እየቀማችሁ ስጡኝ የሚል አደገኛ ስሜት እንዳያድርባቸው እወነቱን ገልጾ ማስረዳት እጅግ ያስፈልጋል።

፬ኛ/ የሰሜናዊው ኢትዮጵያ ክፍሎች መሬት በመሠረቱ የዚያው ሕዝብ ርስት ስለሆነ በዚያ ክፍል የሚኖረው ሕዝብ ለራሱ ለአካባቢው ሕዝብና ለጠቅላላው የሀገር ልማት ሲፈልጉ

ከሚችሉ አንዳንድ ቦታዎች በቀር ርስቴን የሚነካብኝ ይኖራል ብሎ የሚሠጋበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይጠቅማል።

ከዚህ በኋላ ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ። ይኸም ጉዳይ የራሳቸው መሬት የሌላቸው ገበሬዎች በሰላም መሬት የሚያገኙበት መንገድ ነው። ይህም ሲደረግ መንግሥት የሕዝቡን ሰላም አደፍራሽ ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ መሬቱን ወደጁ ሊያዛውርባቸው ይችላል ብዬ ያመንሁባቸውን ዘዴዎች እንመልከት።

፩ኛ/ በመንግሥት ስም የቆዩትን መሬቶች ለርሻና ለግጦሽ የሚሆኑትን ለደን ለማዕድንና ለሌላም ይህን ለመሰለ ነገር ከሚከለሉት እየለየ ጢሰኞች ገበሬዎች በጓድ በጓድ እየሰፈሩ ሊያለሟቸው እንዲችሉ ማድረግ

፪ኛ/ ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ በገንዘብ በመግዛት ወይም በሕግ በመውረስ ሳይሆን በጉልባትና በሥልጣን በመመካት ወይም ይኸን በመሰለ ተንኮል የዘረፉ ሰዎች የያዙዋቸውን መሬቶች በሙሉ ወደ መንግሥት እጅ በቀጥታ ማዛወር።

፫ኛ/ በምንም መንገድ ይሁን ሊያለማ ከሚችለው በላይ መሬት የያዘ ማንኛውም ሰው ለም ለም ከጠፍ ጠፍ የሚባለው የግብር አመዳደብ ደረጃ ጋሻ ሁኖ ሳይጠብቀው ከባድ አዳጊ ግብር እንዲከፍል ማድረግ (ይህ ዓይነቱ የግብር አከፋፈል ለአንድ ድርጅት የቀን ሙያተኞችም ሆነ ቋሚ ሠራተኞች ከሥራቸውና ከድካማቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ በቂ ደመወዝ ከማስከፈል ጋር የሰዎችን ኑሮ ለማቀራረብ ዋና መድኃኒት ሁኖ ስለተገኘ ለሕዝቡ የሚሠራ እውነተኛ መንግሥት ባለበት አገር ሁሉ ይሠራበታል። ስሙ በእንግሊዝኛ ሔቪ ፕሮግሬሲቭ ታክሴሽን ሲባል ዋና ሐሳቡም አንዱ ሰው ገቢው ከፍ ባለ መጠን ወይም የያዘው ማንኛውም ዓይነት ሀብት ሰፊ በሆነ መጠን ከመቶ የሚፈለግበት ግብር ወደ ላይ እያደገበት ይሔዳል ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በርሻ በንግድ ወይም በሌላ ሥራ በዓመት ሐያ አምስት ሺህ ብር አግኝቶ በመቶ አሥራ አምስት ግብር እንዲከፍል ቢደረግ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሐምሳ ብር ለመንግሥት ግብር ከፍሎ ሐያ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሐምሳ ብር ይቀርለታል ማለት ነው። ነገር ግን የዚህ ሰው ገቢ በዓመት መቶ ሺህ ብር ቢሆን ግብሩ ደረጃ በደረጃ እያደገ ስለሚሔድ የሚከፍለው በመቶ ሐምሳ ሁኖ ሐምሳ ሺሁን ለመንግሥት ግብር ከፍሎ ለራሱ ሐምሳ ሺህ ብር ያስቀራል ማለት ነው። በዚህ መንገድ የግብር ክፍያ መጠን እያደገ አንድ ከፍተኛ ገቢ ያለው ሰው ከገቢው በመቶ ሰማኒያ እስከ ዘጠናውን ድረስ ግብር ሊከፍለው ይችላል። ይኸም ሕዝብ መንግሥት መንግሥት ሕዝብ በሆኑባቸው አገሮች ሁሉ እየተሠራበት ያንዱ ኑሮ ወደ ሰማይ ሲጉን የሌላው ኑሮ ወደ እንጦርጦስ የሚወርድበትን ሥርዓት ሊገታውና ሰብአዊ መልክ ሊያስይዘው ችሏል። በሀገራችንም በግድም ሆነ በውድ መለመድ ያለበት ነገር ሲሆን ራሳቸው ሠርተው የማይጠቀሙበትን መሬት የመሰብሰብ ልማድ ያላቸውን ሰዎች ከዚህ ክፉ ልማድ ለማገድና በማይገባ የያዙትንም ለማስለቀቅ ይበጃል።)

፬ኛ/ ከአሁን ጀምሮ መንግሥት ሳያውቅ በየቀበሌው የሚያደርገውን የመሬት ግዥና ሽያጭ በቀጥታ ማገድ ያስፈልጋል።

# ስለ አሠፋፈሩና ስለ አሠራሩ ዘዴ

መንግሥት በኃይል ብቻ ሁሉን ለማስተካከል ቢፈልግ ከሌላው ብዙ ከባድ ችግር ጋር መንገድ ድልድይ መሥራቱ ወታደር ማመላለሱ ስንቅና ትጥቅ መጫኑ ብቻ በገንዘብ በኩል ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ መሆኑ አያጠራጥርም። ወጭ ካልቀረም ወጪው ለሰላማችንና ለልማታችን ቢውል በብዙ መንገድ ይጠቅማል። ይኸም ማለት ባለመሬት ከሆኑ ሰዎች ጋር መሬታችሁን ለጢሰኝኖቻችሁ ልቀቁ ብሎ ለመጣላት ገንዘብ ከማባከንና ቂሙ በቀላሉ የማይሽር ሁከት ከመፍጠር እጅግ በሚቀልና በሚጠቅም መንገድ ጢሰኞችን በአካቢያቸው ከኖሩና ከሚያውቋቸው መሰሎቻቸው ሳይለዩ በጓድ በጓድ እያደረጉ በአዲስና ዘመናዊ በሆነ ዘዴ ሰፋፊና ጤነኛ የሆኑ መንደሮች እየቆረቆሩ ማስፈር ያስፈልጋል ማለት ነው። ለዚህም የሚያስፈልገው፡-

፩ኛ/ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር አሁን ከሚሠራው በላይ በጦሩ ኃይል በቅርብና በቀጥታ እየተረዳ ለግብርና ሥራ የሚውሉትን መሬቶችን እየለየ ለግብርና ሥራ የሚውሉትን መሬቶች እየለየ ሕዝብ የማስፈሩን የማቋቋሙንና ሥራውን የመቈጣጠሩን ኃላፊነት ይዞ እንዲመራ ማድረግ

፪ኛ/ ከዚህ የሚቀድም ችግር ስለሌለ የሀገሪቱ ዓቅም የሚፈቅድ ከሆነ መንግሥት ለዚሁ አንድ ቋሚ በጀት መመደብና ሀገሪቱ ዓቅም ካነሳት እርዳአታና ብርድ በሰጡ ቍጥር አንዳንድ ግዴታ ከሚጠይቁ ኃያላን ሳይሆን እንደ እስካንዲኔቪያን አገሮችና እንደ ዓለም ባንክ ካሉት ድርጅቶች ብድር ጠይቆ ለዚህ ሥራ መመደብ።

፫ኛ/ በቀና አስተሳሰብና በዘመናዊ ዘዴ እየመሩና እየተቆጣጠሩ ካሠሩት የርሻ ሥራ በዓመትና በሁለት ዓመት እንኳ ጥቅም ሊያስገኝ ስለሚችል

ሀ/ እንደ እህል የቅባት እህል ጥጥና እነሱን የመሳሰሉትን የርሻ ውጤቶች በሚመረቱባቸው ቀበሌዎች የሚሰፍሩ ገበሬዎች ከሰፈሩ ከሁለት ዓመት በኋላ ጀምረው መንግሥት ያወጣላቸውን ገንዘብ መክፈል እንዲጀምሩ ማድረግ።

ለ/ እንደ ቡና እንደ ፍራፍሬ ዛፎች ያሉ ተክሎችን የሚያለሙና ከብት የሚያረቡ ገበሬዎች ፍሬዎቹና ከብቶቹ ለገበያ ከሚደርሱላቸው ጊዜ ጀምሮ

የመንግሥቱን ገንዘብ መክፈል እንዲጀምሩ ማድረግ በጢሰኝነት የሚገኙ ገበሬዎችን ከጢሰኝነት ቀንበር ነፃ አውጥቶ በአዲስ ዘዴ የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩና የሀገራቸውን ኢኮኖሚ በሰፊው እንዲደግፉ የሚከናወነውን ተግባር በጣም ሊያፋጥነውና ሊያጠናቅቀው ይችላል። ከዚህም በላይ በርሻ በሚለሙት ቀበሌዎች ሁሉ የየቀበሌው የርሻ ውጤቶች በተለይም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡት እንደየአስፈላጊነታቸው በእንዱስትሪ እየተዘጋጁ የሚቀርብባቸው ቀላል እንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ያስችላል።

፬ኛ/ አሁን በመንግሥት ስም በሚገኝና ከታላላቅ ዘራፊዎች በቀጥታ የሚወረስ ቦታ ላይ ሰፍረው የሚገኙ ጢሰኞች የአሠፋፈራቸውና የአሠራራቸው ዘዴ ዘመናዊነት እንዲኖረው በአዲስ መልክ አደራጅቶ በያሉበት እንዲቆዩ ማድረግ ካንድ ቦታ አንሥቶ ወደ ሌላ አዛውሮ ለማስፈር የሚያስፈልገውን ድካምና የገንዘብ ወጭ ሊያስቀር ይችላል።

፭ኛ/ በዘላንነት የሚኖረው ሕዝብ በአንድ አካባቢ ሰፍሮ ቋሚ ቤት ሠርቶ በዚያው አርሶና ከብት አርብቶ የተሻለ ኑሮ መኖር መቻሉን ማስተማር ያስፈልጋል።

ስለ ባለርስቶች የወደፊት ደኅንነት።

በየከተማው ሁነው ብዙ ጥቅም እያገኙ በተጨማሪ የርሻን ውጤት ከደሀ ጢሰኛ አፍ ሲነጥቁ የኖሩት ብዙ ባያሳስቡም ሌሎች ሊያሳስቡ የሚችሉ ወገኖች አሉ። እንደ ዘራፊዎች ተቈጥረው መሬታቸው በቀጥታ የማይወሰድባቸው ሰዎችም ጢሰኞቻቸው ስለሚወሰዱባቸውና በመሬታቸው የሚከፍሉት ተራና አዳጊ ግብር ስለማይቀርላቸው ለጊዜው ቅር ሊላቸው ይችል ይሆናል። ነገር ግን በለውጡ አምነውበትና አስተሳሰባቸውን ለውጠው ሀገራቸውን በሰላም ለመለወጥ ከተባበሩ በአዲስ ዘዴ ከለመዱት የተሻለ ኑሮ ሊኖሩ ይችላሉ።

፮ኛ/ አንድ ሰው በስሙ ብቻ የሚኮራበት አሥር ጋሻ መሬት ይዞ አንዳንዱን በጠፍነት አቦዝኖ ከሚያስቀምጥ እንዲሁም በከሱ ጢሰኞችና ገበሬዎች ጉልበት ብቻ ተማምኖ ከሚኖር የተወሰነ መሬት ኑሮት ከኅረቤቶቹ ወይም ከወዳጆቹ ጋር ተባብሮ በብድር ከቻለም በራሱ ገንዘብ ዘመናውያን የርሻ መኪናዎች ገዝቶ በተቃለለና በተቀላጠፈ ዘዴ በማኅበር ወይም በወንፈል ቢሠራ የበለጠ ጥቅምና የማይወቀስ ስም ሊኖረው ይችላል።

፪ኛ/ እነዚህ ሰዎች ለለውጡ ተባባሪ ሁነው ሲገኙ ጢሰኞችን ለማስፈርና ለማቋቋም የሚደክመው መንግሥት የነዚህ ወገኖች ኑሮ አቋም እንዳይናጋም አስፈላጊ በሆነው ሁሉ መደገፍና መርዳት ይገባዋል።

ሀ/ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜና ቦታ ሁሉ ለአዲሱ የአሠራር ዘዴ የሚያስፈልጋቸውን ምክርና ትምህርት በመስጠት

ለ/ ሥራቸውን ለማሻሻልና ለማስፋፋት የሚያስፈልጋቸውን ብድር በመስጠት አስደሳችና ጤነኛ የሚሆን አዲስ ሕይወታቸውን እንዲጀምሩ ሊረዳቸው ያስፈልጋል።

ስለ ስሜናዊው ክፍል መሻሻል።

በብዙ አገሮ እንደሚታየው የአንድ አገር መሬት ዓየር የባሕር ክልል እንዲሁም በመሬቱ ላይ በባሕሩ በምድሩ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ሁሉ መንግሥት በቀጥታ የሚያዝበት ነው። ይህም ማለት እንዳለፉት የኛ አገር ዘራፊ- መሪዎች ያቋቋሙት የቅሚያ ድርጅት ያለ መንግሥት እያዘዘበት አብዛኛው ሕዝብ በሚያሠቅቅ የችግር የበሽታና የድንቁርና መከራ ሲማቅቅ ጥቂት ሌቦች ያለልክና ያለ ገደብ ይፈነጩበታል ማለት አይደለም።

በነዚያ አገሮች አስተሳሰብ አንድ ነገር የመንግሥት ነው ሲባል ከአንድ አገር ሕዝብ ውስጥ ጥቂቶቹ ብቻ እንደፈለጋቸው የማያዙበት የጠቅላላው ሕዝብ ቋሚና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ሀብት ነው ማለት ነው።

እንግዲህ የሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍለ - ሀገሮች መሬት ቀደም ሲል ደጋግሜ እንደገለጽሁት የማይሸጥ የማይለወጥ የኗሪው ሕዝብ ቋሚ ርስት ስለሆነ በመሠረቱ የመንግሥት መሬት ነው ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም መንግሥት ማለት ሕዝብ ሕዝብ ማለት መንግሥት ነው።

ሁኖም ለሕዝቡ ጥቅምና ለዘመናዊ አሠራር ሲባል በስምምነት ሊደረጉ የሚገቡ አንዳንድ ለውጦች መደረግ አለባቸው።

፩ኛ/ በየትም ቢሆን የአንድ አገር የምድር ውስጥና ከምድር በላይ ያሉ ሰፊ ሀብቶች ማለት ደን የዱር አራዊት ወንዞች ተራሮችና የማዕድን ሀብት የመንግሥት ናቸው። (ማለት ሀብቱ የተገኘበት ቀበሌ ተወላጆች ብቻ ሳይሆን

የመላው የሀገሩ ተወላጆች ሀብት ነው።) ይህ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹም

ሀ/ በአንድ አካባቢ የሚገኝ የአንድ አገር የማዕድን ሀብት በካፒታሊስ አገሮች (ማለት የግል ሀብትን ለማዳበር ነጻ ውድድር እንዲሁም ማጭበርበርና በሚቻል መጠን ሠራተኛን ተጭኖ ራስን ማከበር የፈለጉትን ሥራ መርጦም የመጀመር ለያንዳንዱ ግላዊ ሰው ዕድል ባላቸው አገሮች) አብዛኛውን ጊዜ በአንድ የብዙ ሀብታሞች የንግድና የእንዱስቲ ማኅበር ወይም በአንድ ታላቅ ከበርቴ በሆነ ቤተ ሰብ በሚመራ ድርጅት እንዲያዝ ሲደረግ አልፎ አልፎ በመንግሥትም ሊያዝ ይችላል።

ለ በሶሽያሊስ አገሮች (ማለት «ኮሚኒስት ፓርቲ» የሚባል አንድ ማኅበር ብቻ የሚመራው መንግሥት ሁሉንም ነገር በቀጥታ በሚቈጣጠርባቸው እያንዳንዱ ሰው ወይም አንድ ጓድ በግሉ የሚካሔድባቸው የሥራ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ በማይቻልባቸው አገሮች) እንደማንኛውም ነገር ሁሉ በመንግሥት የተያዘ ነው።

እንዲሁም ደኖችና የዱር አራዊት በሚገባ ተጠብቀው ሀገሩን በብዙ መንገድ እንዲጠቅሙ አስፈላጊ የሆነውን ጥንቃቄና ቁጥጥር ማድረግ በየትም ዓለም ቢሆን የመንግሥት ተግባር ነው። ወንዞች አስፈላጊ ሁኖ በተገኘበት ቦታ ሁሉ እየተገደቡ ለአካባቢው ሕዝብ የመስኖ ልማት የኤሌክትሪክ ኃይልና ብርሃን እንዲጠቅሙ ማድረግና በጠቅላላው የአንድ አገር መሬት በጎርፍ በመታጠብ በዛፎች ያለ አግባብ በመጨፍጨፍና ይህን በመሳሰሉ ባለማወቅ ወይም በግዴለሽነት በሚደርሱ ጉዳቶች ሀገር እንዳትራቆት መቆጣጠርም የመንግሥት ኃላፊነት ነው። ይህ እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት እነዚህን የመሳሰሉ ታላላቅ ብሔራዎ ተግባሮች የተለየ የሀብት ይዞታ በሌላቸው ግላውያን ሰዎች ዓቅም ብቻ ሊፈጸሙ ስለማይችሉ ነው።

እንግዲህ ሕዝብ ይኸን ተገንዝቦ በሕዝብ የተቋቋመ መንግሥት የሚጠይቃቸውን ተገቢ ጥያቄዎች ሁሉ ያለማመንታት ማሟላት አለበት ማለት ነው።

፩ኛ/ የአካባቢውን ሕዝብ ወይም የሀገሪቱን ሕዝብ በጠቅላላው ሊጠቅም የሚችል ብሔራዊ ሀብት ያለበት ቦታ ሁሉ የመላዋ ኢትዮጵያ ሀብት ስለሆነ የትም ቢሆን መንግሥት ሊያዝበት ይገባዋል።

፪ኛ/ መንግሥት የአካብቢውን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል የርሻና የርቢ ሥራዎችን ሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎች ለማቋቋም በሚፈልግበት ጊዜ በየትኛውም ቀበሌ አስፈላጊ የሆነውን መሬት የማግነት መብቱ በማንም ዘንድ ሊታወቅለት ያስፈልጋል።

፫ኛ/ የአካባቢውን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻልና የተሟላ ለማድረግ ለሚከፈቱ ሕዝባዊ መገልገያዎች ማለት ለመንገድ ለትምህርት ቤት ለክሊኒክ ለሆስፒታል ለገበያ ለመናፈሻና እነሱን ለመሰሉ ሁሉ የሚፈልገውን መሬት በቀጥታ የመውሰድ መብት አለው።

፬ኛ/ በአንዳንድ ሰፋፊና የተለየ ሁኔታ ባላቸው ክፍሎች ለምሳሌ በሰሜንና በጌምድር ክፍለ ሀገር እንደነ መተማና ሰቲት ሁመራ በጎጃም እንደነ መተከል ባሉት ቦታዎች ለከፍተኛ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት የሚፈልገውን መሬት የማግኘት መብት አለው።

# የሕዝቡን አሠፋፈርና የአሠራር ዘዴ ስለመለወጥ

በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖረው ሕዝብ ከደቡቡ ክፍል በመጠኑ ለየት ባለ ሁኔታ በየቀቤውና በየሰበካው ተፈነጣጥረው በሚገኙ መንደሮች ተበታትኖ ይገኛል። የያንዳንዱ ገበሬ ማሳዎችም በአንድ ላይ ተጋጥመው የሚገኙ ሳይሆኑ በየጎጡ የሚገኙ የመሬት ትልታዮች ናቸው። ይህ ዓይነቱ የአኗኗር ልማድ እስከ ዛሬ እንደነገሩ ሁኖ ለኖረው እናት አባቱ አያት ቅድመ አያቱ ተወልደው በኖሩበት ቦታ ተወልዶ ኑሮ ከዚያው ሳይወጣ መሞቱንና መቀበሩን እንደ ከፍተኛ ክብር ለሚቈጥረው ሕዝብ ስሜቱን የሚያረካ ጠባይ ኑሮት ቢቆይም ገጠሬውና ለፍቶ አዳሪው ኢትዮጵያዊ የከተማ ኗሪዎች ከሚያገኟቸው ዕድሎች ምኑም ሳይጎድልበት በዕድገት እንዲራመድ አዲሷ ኢትዮጵያ ለምታደርገው የወደፊት ሰፊ ጥረት እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ሕዝቡ

ለራሱ ዕድገትና ደኅንነት ሲል የአኗኗርና የአሠራር ዘዴውን በፍጹም መለወጥ አለበት።

፩ኛ/ ቢያንስ ቢያንስ የአንድ ሰበካ (አጥቢያ) ሕዝብ ለመንደር አሠራር ምቹ መሆኑ በተጠና አንድ አካባቢ በዘመናዊ ዘዴ መለስተኛ ከተማ የሚሆን መንደሩን ሠርቶ መስፈር እጅግ ይጠቅመዋል ይህም ማለት በመጀመሪያው አነስተኛ የመሻሻል ደረጃ

ሀ/ በራሱና በመንግሥቱ መረዳዳት በአካባቢው ለሚሠራ መንገድ አቅራቢያ በመሆን በግብርና ሙያ ያፈራውን የርሻ ውጤት በቀላሉ ለገበያ ማቅረብና ጥቅሙን ማሻሻል ይችላል።

ለ/ የታመሙ ሰዎች ወይም በምጥ የተያዙ ሴቶች ብዙ መንገላታት ሳይደርስባቸው በቅርቡ መኪና አግኝተው ወደ ሕክምና ቤት ሊደርሱ ይችላሉ።

ሐ/ ለሰው ወይም ለከብት ክትባትና ሕክምና ለሌላም ይህን ለመሰለ እርዳታ መንግሥት የሚልክለት ነገር ሁሉ በቀላሉ ሊደርስለት ይችላል።

፪ኛ/ ከጎረቤቶች ጋር ተባብሮ ለመሥራት

ሀ/ በማኅበር ለማረስ ከብት ዶሮ ንብን ሌላም እንስሳት ለማርባት

ለ/ ከበር ላይ ትምህርት ቤት ክሊኒክ እንዲሁም የፈለጉትን ነገር ሁሉ የሚገዙባቸው ሱቆች ለማግኘት

ሐ/ ወህና መብራትን የመሳሰሉ ነገሮችን ለማስገባት።

መ/ በምክክርና በኅብረት ለርሻና ለግጦሽ የሚሆኑትን መሬቶች በመለየት የርሻና የርቢ ሥራዎችን ዘመናውያን ለማድረግ

ሠ/ በኅብረት የአካባቢን ጽዳትና የግል ንጽሕናን ለመጠበቅ

ረ/ በኅብረት የአካቢን ሰላምና ፀጥታ እየጠበቁ ሥርቆትን ግዳያንና እነሱን የመሰሉ ወንጀሎችን ከሀገር ጨርሶ ለማጥፋት ጠቅላላው ማኅበራችን ለሚያደርገው ትግል የራስን ድርሻ ለማበርከት

ሰ/ ወንዞችና ምንጮች ወይም የተፈጥሮ ሐይቆች በማይገኙባቸው አካባቢዎች በመንደሩ ኗሪዎችና በመንግሥት ተራድኦ ለሰውና ለከብት እንዲሁም ለአትክልት ሥራ የሚውል በቂ ወሀ ሊሰጡ የሚችሉ የወሀ ጉድጓዶችን ለማስቆፈር እንዲሁም ለሰውና ለከብት መጠጥ ዓሣዎችን ለማርባት የሚጠቅሙ ሰው - ሰራሽ ሐይቆችና ጉድጓዶች ለመቆፈር ሌሎችንም ይህን የመሰሉ አንድን ሕዝብ በአካልም በአእምሮም የሚያደረጁ ተግባሮችን በተባበረ ጉልበት ለማከናወን ፍቱን መድኃኒት የሚሆንና በብዙ አገሮች እየተሠራበት የሚገኝ ነው። በደቡብ ክፍል የሚገኘውን ጢሰኛ ገበሬ በመንግሥት እቅድ መሠረት በዘመናዊ መልክ ማስፈር ስለሚቻል ይኸ ሁሉ ነገር ብዙ አስቸጋሪ አይሆንም።

# የማስተማሪያው ዋና ዘዴ

የሥልጣኔ ፋና ርቆት የኖረ አንድ ሕዝብ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ መብትንና ጥቅሙን በትክክል እንዳያውቅ ተደርጎ በደንቆሮነትና በጭካኔ በደነዙ ሹማምንት ሲሠቃይ የኖረ ሕዝብ በርግጥ ከመንግሥት ጎን ነገር ይመጣልኛል ብሎ ለማመን እንኳ ይጠራጠር ይሆናል። አይፈረድበትም። አስተዳደር ፍትሕና ርትዕ ማጣት ብቻ ሳይሆን ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች እየተባለ በየጊዜው ከወጣው ገንዘብ አብዛኛው ተበልቶበታል። ጉልበቱ በከንቱ ባክኖ ቀርቷል። ከመንግሥት በኩል ስለሚመጣ ምንም ዓይነት እርዳታ በመንፈሱ ቀርጾት የነበረውን ቅን አስተሳሰብ ተስፋ ከመቁረጥ ጋር ለውጧል። ነገር ግን አሁን ወደ ሌላ የታሪክ ዘመን መሸጋገራችንንና ንጉሡ ነገሥቱ ከነዘረፋ ማኅበራቸው የተወገዱትም ባለፈ ክፉ ሥራቸው በመጠላታቸው ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ሕዝቡ አጥቶት የኖረውን ብዙ መልካም ዕድል በአፋጣኝ መንገድ እንዲያገኝ ለማድረግ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል።

ይኸም ሁኖ ሕዝቡን ይህን ሥራ እያሉ በመንገር ከመወሰንና ለማስገደድም ከመሞከር ይልቅ ሌላ ዘዴ መፈለጉ የበለጠ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል።

ለምሳሌ መንግሥት የአንድን ወረዳ አስተዳደር ሕዝብ ኑሮ ለመለወጥ በብዙ መንገድ ከሚደክም በዚያ ወረዳ ውስጥ አማካይነትና ለሥራው ምቹነት

ያለው አንድ ሰበካ (አጥቢያ) መርጦ። ከሕዝቡ ጋር በተቻለ መጠን በመግባባት በሚፈለገው መንገድ በአንድ አካባቢ ሠፍረውና ከመንግሥት ከሚደርስባቸው እርዳታ ጋር ኑሯቸውን ለውጠው እንዲገኙ ቢደረግ እነሱን በማየት ብቻ የዚያ ወረዳ ሕዝብ በሙሉ ከምንም የበለጠ ትምህርትና በመንግሥት ቅን ፕሮግራም የማመን ዕድል በቀላል ሊያገኝ ይችላል።

ከዚያ በኋላ የሚፈጠውን «የኔ እበልጥ እኔ እበልጥ» የመንፈሳዊ ቅናት ውድድር መገመት አያዳግትም።

ይህም ማለት ሕዝቡ በአካቢው የራሱን ኑሮ እጅግ ወደ ተሻለ ሁኔታ የሚለውጥ ዘዴ በሥራ ላይ ውሎ ካየ ያለ አንዳች ማመንታት ወደ ጋራ ትግሉ ይገባል ማለት ነው።

# የተለየ ኃላፊነት ያለባቸው ክፍሎች

ጠቅላላው ሕዝብ ጉዳዩን በትክክል ከተረዳው ምን ጊዜም ቢሆን የራሱ ተቃዋሚና የገዛ ዕድሉ ተቀናቃኝ ስላይደለ ፍጹም ተባባሪነቱን እንደሚያሳይና ተባብሮም እንደሚሠራ ሳይታለም የተፈታ ነው።

ነገር ግን የለውጡን ዓላማ ለማስረዳት መሞከር ብቻ ሳይሆን በሐሰተኛ ወሬ ሕዝቡን ለማወናበድ የሚፈልጉ አንዳንድ ወስላቶችን የተንኮል ወሬ ለመከላከል እንዲሁም አስናፊና ወደ ኋላ ጎታች የሆኑ ባሕሎችን የማጥፋት ኃላፊነት ያለባቸው ክፍሎች አሉ።

፩ኛ/ መንግሥት የለውጡ መሪ ስለሆነ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት

ሀ/ እጅግ የተመረጡ አስተዳዳሪዎችን የፖሊስ አዛዦችን ዳኞችንና ሌሎችንም የሕዝቡን መብት ፀጥታና ሰላም ለመጠበቅ የልማቱን ሥራና አንድነቱን ለማጠንከር ከልብ የሚሠሩ ሰዎችን ለየቀበሌው መላክ

ለ/ እንደ አጥቢያ ፍ/ቤት ም/ወረዳ አስተዳደር ያሉትን የሥራ ማስፈቻ መሥሪያ ቤቶች በቀጥታ መዝጋት

፪ኛ/ ከሀገሪቱ በጀት ከፍተኛውን ለልማት ሥራ በተለይ ለርሻ ሥራ ዕድገትና መስፋፋት መመደብ ይገባዋል።

ሀ/ ከፍተኛም ሆነ መጠነኛ የርሻ ሥራ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች በሙሉ የሚገባቸውን ደመወዝ እየከፈለ የሀገሪቱን የተፈጥሮና የአካባቢ ሁኔታ ተከትሎ የርሻን ሥራ ለማሻሻል ለሚደረጉ ምርምሮች በተቋቋሙና በሚቋቋሙ ኢንስቲቱቶችና በየቀበሌው ተሰራጭተው የተሻሻለ የግብርና ዘዴን እንዲያስገኙና ለሕዝቡ እንዲያስተምሩ ያሉን የርሻ ትምህርት ቤቶቻችንም እንዲስፋፉ ማድረግ

ለ/ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ የርሻና የርቢ ሙከራ ጣቢያዎችን ማስፋፋት

፫ኛ/ ለገበሬዎች ሰፊ የገበያ ዕድል ለማስገኘት መጣጣርና ያገር ውስጥ ችግራቸውን ማስወገድ

ሀ/ በርሻ ሥራ በለሙ ቀበሌዎች ሁሉ ከሕዝቡ ጋር በመተባበር ቢያንስ ቢያንስ የበጋ መንገዶች ባስቸኳይ እንዲሠሩ ተቀዳሚነት መስጠት

ለ/ ለሀገር ውስጥ ገበያ በሚውሉ የርሻ ውጤቶች ላይ ሁሉ እንደየ አካባቢው የመገናኛ ሁኔታና የሠራተኞች የድካም መጠን እንዲሁም እንደ ሸማቹ ዓቅም ታይቶ በሚተመነው መሠረት ጥብቅና ፍጹም የሆነ የዋጋ ቁጥጥር ማድረግ

ሐ/ በውጭ ገበያዎች በሚያጠራጥር ሁኔታ ተፈላጊ የሆኑ የርሻ ውጤቶች በብዛትም ሆነ በጥራት በየዓመቱ በሰፊው እንዲጨመሩ ገበሬዎችን መምከር ማበረታታት መርዳትና በአንዳንድ ጮሌ አስመጭና ላኪ ነጋዴዎች እንዳይበለጡ በጥብቅ መቆጣጠር።

መ/ ለሰራተኞቻቸው ተገቢውን ደመወዝ እንዲከፍሉ የአካብቢውን አነስተኛ ገበሬም እንዳይጫኑ እየተቆጣጠሩ ሰፋፊ የግል እርሻ ያላቸው ኢትዮጵያውያንም የግል ሥራቸውን ለማስፋፋት ሌሎችም ይህን መሳዩን ሥራ ለመወጠን የሚያደርጉትን ጥረት አለማደናቀፍ ያስፈልጋል።

# ፪ኛ ቤተ ክርስቲያናችን ኃላፊእነት አለባት

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስቲያን መሆን ብቻ ሳይሆን ሕይወቱ በሙሉ ተቆራኝቶ የኖረው ከቤተ ክርስቲያኗ ጋር ነው። ይህ በመሆኑ በቤተ ክርቲያን ስም የመጣ ማንኛውም ነገር ክፉነቱና ደግነቱ ልማቱና ጥፋቱ እውነትነቱና ሐሰትነቱ ሳይመረመር ሙሉ ተቀባይነት እያገኘ ሕዝቡን ሲበድል የኖረ ብዙ ከንቱ ልማድ በሀገራችን ተንሠራፍቶ ይገኛል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን የራሷን አቋምና የልጆችዋን ኑሮ ከሐያኛው መቶ ዓመት አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን ከራሱ ከቤተ ክርስቲያን መሥራች ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ውጭ አድርገዉት የሚገኙ ተረቶችን በቅዱስ ሲኖዶስ እየወሰነች ማስወገድ አለባት።

ሀ/ የበዓላትን ብዛት ባስቸኳይ ቀንሳ ለመላው ተከታዮቿ ማወጅ

ለ/ በየከተማውና በየገጠሩ በሚገኙ አድባራት እየተዘዋወሩ ከክርስቶስ ትእዛዝና ትምህርት እንዲሁም ከተዋሕዶ ሃይማኖት ቋሚ ሥርዓቶች ውጭ በሆነ የውሸት ትምህርት ሕዝበ - ክርስቲያኑን ሲያደናግሩት ሥራውን እንዳይሠራ ሲገዝቱ የሚውሉ አጭበርባሪ ሰመ - ባሕታውያንን ከኦርቶዶክስ ክርስቲያን አባልነታቸው ላይታ በየደብሩ እንዲታወጅባቸው ማድረግ

ሐ/ በደቡባዊ ኢትዮጵያ ክፍል ስሙ ለቤተ ክርስቲያን ሁኖ አብዛኛውን ጊዜ መሳፍንት መኳንንትና ወይዛዝር ወይም ሌሎች ገፋፊዎች የቅስና የዲቁና የድብትርና የግብዝና የዚህ የዚያ እያሉ ይዘው ሲጠቀሙበት የኖሩትን ለስሟ ማጥፊያ ብቻ የተቀመጠ መሬት በቀጥታ ለመንግሥት ማስተላለፍ

መ/ ሳታስተምር በክህነት ባሕር ያጥለቀለቃቸውን ማኃይምናን ካህናቶቿንና ሕዝቡን ለልማትና ለአዲስ አስተሳሰብ እንዲነቁ በሚደረግላቸው ድካም ተቀዳሚ አርአያ መሆን

ሠ/ ከልክ በላይ በመጾምና እርሱን በመሰሉ እውነተኛው የክርስቶስ ትእዛዝ በማይፈልግብን አድካሚ መከራ የሚንገላቱ ብዙ መኃይምናን ክርስቲያኖችን ድካም የሚያቃልል መንገድ መፈለግና ይህን የመሳሰሉ ጉድለቶችን ማረም በዘመናችን ለሚፈለገው ፈጣን የለውጥ እርምጃ ከፍተኛ አገልግሎት ከማበርከቷ በላይ የሀገሪቱን ነጻነት በልጆቿ አማካይነት

በመከላከል ኢትዮጵያ በአፍሪካ አገሮች በሙሉ የማይገኝ የራሷ ፊደል ከባዕድ ተፅዕኖ ፍጹም ነጻ የሆነ ከፍተኛ የዜማ የቅኔና የሥነ - ጽሑፍ ቅርስ እንዲሁም ታላላቅ ታሪካውያን ቦታዎች አስደናቂ የሕንጻ የስዕል የመጻሕፍት ሀብቶች እጅግ ከፍተኛ የሆኑ የሥነ - ምግባርና የማኅበራዊ ኑሮ ግዴታዎች የመፈጸም ኃላፊነቶች ከብዙ እኒህን ከመሰሉ ተግባሮች ጋር እንዲኖሯት ኃላፊነቱን ሁሉ ተሸክማ አቆይታ ለማስረከቧ የሚከፈላትን የግፍ ዋጋ መሰደብን - መወቀስን ባንዳንድ ምኑንም ስያውቁ ለጉራና ለአለ - ይበሉኝ ብቻ የሚቃጁ አጭበርባሪዎችን ቅርሻት ሁሉ መቀበልን በድፍረት ለማስወገድ ያስችላል።

# ፫ኛ ወጣቶች ታላቅ ኃላፊነት አለባቸው

ሀ/ ለሁከት ለውጭ አይዲኦሎጂ ማስፋፊያና ለግል ፍላጎታቸው ማሟያ መሣሪያ ሊያደርጓቸው በሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች የሐሰተኛ ተስፋ ስብከት (ዴማጎጂ) ወጥመድ ሳይወድቅ ሀገራቸው በራሷ መንገድ ከሚፈለገው ፍጹም ለውጥ ለምትደርስበት ዓላማ ቢሠሩ ከፍተኛ ድርሻ ያበረክታሉ።

ለ/ ነገ ሀገሪቱን ደኅና ብትሆን ከነደኅነቷ በችግር ላይ ብትሆን ከነችግሯ በሙሉ ኃላፊነት የሚረከቧት ራሳቸው መሆናቸውን አምነው ለሀገራቸው ደኅንነት በሙሉ ልብና ቆራጥነት ሊሠሩላት ይገባቸዋል፡

ሐ/ አንድ አፍሪቃዊ መሪ እንዳሉት ሁሉ በምዕራብም ሆነ በምሥራቅ የባዕድ አይዲኦሎጂ ተጠምዶ መያዝ የሀገሩን ስረ - ወጥ የተፈትሮ አስተዋይነት ከመደምሰሱ በላይ በአንዱ አገር የተሠራውን በሌላው በቀጥታ ለመገልበጥ ሲሞክር የሚያስከትለውን አደገኛ ውጤት ተረድተው የሀገሪቱን ችግሮች በተለይም የመሬት ይዞታን በዘዴና በሰላም ለመለወጥ ያለውን ችግር ለማስወገድ «መሬት ለአራሹ» የሚል ዘዬን (ስሎጋን) በመዘመር ብቻ ሳይሆን በሚያዋጣው መንገድ ተባብረው ሊሠሩ ይገባል።

# ፬ኛ እያንዳንዱ ያገር ቤት ኗሪ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት

ሀ/ በሆነ ባልሆነው ምክንያት ሙግት እየፈጠሩ ለሥራ የሚውል ጉልበትና ጊዜያቸውን ወደ ፖሊስ ጣቢያዎችና ፍርድ ቤቶች በመመላለስ ደክመው ያፈሯትን መጠነኛ ሀብት በጉቦ ስለሚያባክኑ ዐዋቂዎች ሥልጡኖችና ብርቱዎች የሆኑ የሚመስላቸው ሰዎች ሁሉ ጊዜ ያለፈባቸው በአዲሷ ኢትዮጵያ ምንም ግምት የማይሰጣቸው የዋሆች መሆናቸውን መረዳት አለባቸው።

ለ/ የጅ ባለሙያዎች በየትም ዓለም እጅግ ተከብረው ሙያቸውንና የሥራ ዘዴያቸውን እያሻሻሉ የየሀገራቸውንና በጠቅላላውም የዓለምን ሕዝብ ኑሮ በፍጹም ለመለወጥ ዕድል ሲያገኙ በኛ ሀገር ርስትን የጋብቻ ግንኙነትን ከዚህም አልፎ በሙሉ ሰውነት መታየትን እየተከለከሉ ኢትዮጵያ የሰነፍ ዘር ቈጣሪዎችዋ መቀለጃ የሥርቶ አዳሪዎችዋ መቆራመጃ ሁና የቆየችበትን ርኩስ ወግ በኅብረት መደምሰስ ያስፈልጋል።

ሐ/ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለሀገሩ ችግርም ሆነ ደኅንነት የየራሱ ድርሻ ያለበት መሆኑን አምኖበት ራሳችን ራሳችንን የምንፈራበት የሹክሹክታ ወሬና ሐሜት በገዛ ራሳችን ላይ እየፈጠርን የራሳችንን ጥላ በማየት እየደነበርን እኛ የማናመጣው ችግርና ጥፋት ከመሬት እንደ እንጉዳይ የሚበቅልብን ከሰማይ እንደ መብረቅ የሚወርድብን ይመስል ስለራሳችን ጥፋት ራሳችን የምንፈጥረውን ልብ ወለድ ታሪክ ማሾክሾኩን ትተን መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአንድ እናት እንደ ተወለደ ቤተ ሰብ አድርገን በማየት ያለብንን ችግር ሁሉ በወንድማማችነት እየተወያየንበትና በኅብረት እያስወገድን መሥራት ያስፈልገናል።

# ግባችን

የተነሣሁበት ዋና ርእስ የመሬት ይዞታን ሥርዓት ለመለወጥ ይረዳል ብዬ በራሴ በኩል ያመንሁበትን አስተያየት መግለጽ ቢሆንም ከዚሁ ጋር ግንኙነት

ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ለጠቅላላው ለውጣችን ሊጠቅሙ የሚችሉ አንዳንድ አስተያየቶችን ጨማምሬያለሁ።

ከዚህም ላይ ስለጠቅላላው የለውጣችን ዓላማ ጥቂት ልገልጽ እፈልጋለሁ። ሕልማችን የዓለም ቅን ሕዝብ ሁሉ ሕልም ነው።

የኛ ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም ሕልም የሆነ ታላቅ ግብ አለ። ይህም ግብ ምድራዊ ገነት ፈጥሮ የሰው ልጆች ከችግር ከበሽታ ከድንቁርና ነፃ ወጥተው ወንጀል እሥራት ጭቆና ግፍ የኑሮ ጭንቀት ተረስተው የሰው ልጆች በፍቅርና በደስታ እንዲኖሩ ለማድረግ መጣጣርና ሲሆን ብዙ ሀገሮች ከዚያ ገነት በመጠኑ ቀረብ ብለው አሁንም እርምጃቸውን እያፋጠኑ ወደዚያው ጨርሶ ለመግባት በመገስገስ ላይ ናቸው።

እኛ ግን ከገነቱ ቀርቶ ከመካነ - ንስሐው ሳንደር ገና በሲኦል ውስጥ ሁነን ስንሠቃይ እንገኛለን።

በሥልጣኔ ወደፊት ከገፉት አገሮች ጥቂቶችንም ሆነ ብዙዎችን የምዕራቦችንም ሆነ የምሥራቆችን ያየ አንድ ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሰው ነው የሚኖረው ብሎ ማመን እጅግ ያስቸግረዋል። እኛ የምንኖረው በቁም መቃብር ውስጥ ነው። የመጀመሪያ ተግባራችንም መግነዛችንን ቀዳደንና በጣጥሰን የተጫነብንን የመቃብር ድንጋይና አፈር ፈነቃቅለን ወደ ብርሃን ዓለም መውጣት ሲሆን ለዚህም የተባበረ ክንድና ኃይል ያሻልና።

ከዚያም በተባበረ ኃይላችን የራሳችንን ገነት ለመፍጠር «ሀ» ብለን እንጀምራለን። በቆራጥነት እንራመዳለን። በምንፈጥረው ገነት እኛ አሁን ያለነዎች ሰዎች ገብተን ልንንቧችበት መጓጓት የለብንም። ለዚህ ብንታደል ኑሮ አባቶቻችን እኛ ያገኘነውን ዕድልና ድል ያገኙልን ነበር። እኛ ለዚህ አልተመደብንም አምላክ እኛም የመደበን «እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል» ያለቺውን የአሕዮች ፈላስፋ ትምህርትና «ከራስ በላይ ነፋስ» የሚለውን የበሰበሰ ምሳሌ አነጋገር ከወደቀው የኑሮ ሥርዓታችን ጋር ደምስሰን «እያንዳንዱ ትውልድ ዓለምን እሱ በተረከበት ጊዜ ከነበረችበት ሁኔታ እጅግ የተሻለች አድርጎ ለተተኪው ትውልድ የማስረከብ ኃላፊነት አለበት።» የሚለውንና ብዙ ፈላስፎች የተስማሙበትን ቁም ነገር ፈጽመን አንድ የተሻሻለች አገር ለትውልዳችን ለማስረከብ ነው።

ከዚህ ላይ በታላቅ ምሳሌነቱ የማንኛውም አገር ሰው የሚጠቅሰውን የአንድ የዓረብ ሽማግሌ ታሪክ ልጠቅሰው እፈልጋለሁ። ታሪኩም የሚከተለው ነው።

ዘጠና ዓመት ዕድሜ የነበረው አንድ ዓረባዊ ሽማግሌ በጓሮው የተምር ዛፍ ችግኞች በትጋት ይተክላል። አንድ መንገደኛ ይህን ሥራ ሲያይ በነገሩ ይደነቅና መንገዱን አቋርጦ ወደ ሠራተኛው ሽማግሌ ሔዶ «በዚህ የርጅና ዘመንህ በማረፍ ፈንታ እነዚህን የተምር ችግኞች በመትከል የምትደክመው መቼ ደርሰውልህ ልትጠቀምባቸው ነው?» ይለዋል።

ሽማግሌውም በመንገደኛው ሰውዬ ሞኝነት ስቆ «እኔ ስበላው የኖርሁት ተምር እኔ ሳልሆን አያት ቅድም አያቶቼ የተከሉትን ነው። ከነሱ የወሰድኩትን ዕዳም ለልጅ ልጆቼ መክፈል ስላለብኝ ለነርሱ እተክልላቸዋለሁ» ሲል መለሰ ይባላል።

ሽማግሌው እንዳለው ሁሉ የሰው ጠቅላላ ሕይወት በማያቋርጥ ረጂም ገመድ የተቀጣጠለ በመሆኑ አንድ ትውልድ ላለፉት ትውልዶች ባለ ዕዳ እንደመሆኑ መጠን ለሚተካው ትውልድ  አሳሳቢ የሆነ የውለታ ዕዳ ትቶ የማለፍ ግዴታ አለበት። በተለይም እንደኛ ቅድመ አያቶች በሀገሩ ያገኘው ጥቅም ለሀገሩ ካፈሰሰው ላብና ደም በምንም የማይመጣጠን የሆነ ብዙ ሕዝብ ስለሌለ ያባቶቻችን ባለዕዳዎች ነን።

በዚህ ካላመንና «እኔ ዕለተ - ምፅዓት እኔ የምሞትበት ዕለት ነው» አለ በሚባለው ራሱን ብቻ ወዳጅ ሰው እምነት ከተጓዝን ምስኪን ኢትዮጵያ የድኩማን የለማኞች የረኃብተኞች የደንቆሮዎች በሌላም በኩል የጨቋኞች የዘራፊዎች የቀማኞች የወንጀለኞች አገር እንደሆነች ትቀያለች። እንደዚያው ሁነው እንዲኖሩ የምንፈርድባቸውም ከራሳችን በላይ እንወዳቸዋለን የምንላቸው የያንዳንዳችን ልጆችና የልጅ ልጆች ይሆናሉ። ለየራሳችን ልጆች ደኅንነት ብቻ እንጥራለን ብለን ራሳችንን ብናሞኝ ደግሞ የአንድ አገር ሕዝብ በአንድ ላይ እንዲሻሻል ካልተደረገ በሐያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብዙዎቹን በአዘቅት ውስጥ ጥለው ራሳቸው ብቻ በምቾት መፈንጨት ለሚፈልጉ ጥቂት ጮሌዎች ምንም ቦታ የሌላቸው መሆኑን መዘንጋት ይሆንብናል። ለዚህም ምሳሌ፡- ወደሩቅ ቦታ ወደ ሩቅ ዘመን ሳንሔድ በዓይናችን ያየናቸው ለሠላሣ ሶስት ዓመታት ሀገራቸውን በጉድ አዘቅት ውስጥ ጥለው ኑረው በመጨረሻው

በራሳቸው ሥራ በጉድ አዘቅት ውስጥ የወደቁት የኛን የድሮ ገዥዎች ማስታወስ ይበቃል።

እንግዲህ የነገሩ ሁሉ ውጤት እንዲህ መሆኑ ከታወቀ ዘንድ የየግል ምኞታችንንና ፍላጎታችንን ከሀገራችን ጠቅላላና ዘላቂ ጥቅም ሳናስቀድም መሥራት ብቻ ሰላም ብልጽግና ፍቅርና የኑሮ ዋስትና የሚሰጠን ኃይል ነው ማለት ነው።

## ወደ ግባችን የምንጓዝባቸው መንገዶች።

ወደ ምንፈልገው ግብ ለመድረስ የሚረዱን ብዙ የሥራ ዘርፎች አሉ። ሁኖም በቅድሚያ የሚያስፈልጉን ስላሉ የቀሩትንም ደረጃ በደረጃ የሚመጡ ስለሆኑ በሥራ ቅደም ተከተል በኩል ብርቱ ጥንቃቄ ልናደግ ይገባል።

በዚህ ሁኔታ የአገራችንን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን የቱን የሥራ ዘርፍ ልናተኩርበትና የሚበልጠውን ገንዘብ ልናውልበት ይገባል? ብለን ስንጠይቅ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁትና ብዙ ሰዎችም እንደተናገሩት እርሻ ያለጥርጥር ተቀዳሚውን ቦታ ይዞ ይገኛል።

ይህ ይሆነባቸው ምክንያቶችም የሚከተሉት ናቸው።

፩ኛ/ ሀገራችን ለርሻና ለርቢ ሥራ ምቹ የሆነ በጣም ብዙ ቦታ አላት።

፪ኛ/ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ከሚገኙ የእህልና የየዕለቱ ምግብ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት የእህልና የአትክልት ዓይነቶች ብዙዎቹ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ሊበቅሉና ሊዳብሩ ይችላሉ።

፫ኛ/ በወጉ ይዘን ከሠራንበት የከብት እርባታ ሥራችን በዓለም ውስጥ በሥጋና በወተት ከታወቁት ጥቂት አገሮች ኢትዮጵያ አንዷ እንድትሆን ሊያደርጋት ይችላል።

፬ኛ/ የንብ እርባታ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል ሊስፋፋ የሚችል ሥራ ነው።

ከዚህ በኋላ እነዚህን ሥራዎች በዘመናዊ መልክ አደራጅተን ብናራምዳቸው ምን ያህል ተፈላጊነት እንደሚኖራቸው ይህ የሚሆንባቸውን ምክንያቶች እንመልከት።

፩ኛ/ የዓለም ሕዝብ ቍጥር በየቀኑ እየጨመረ ሲሔድ የዓለም የርሻ ውጤት እኩል እየጨመረ ባለመሔዱ የምግብ እጥረት የአህኑንና የወደፊቱን የዓለም ሕዝብ እጅግ ከሚያሣጉት ታላላቅ ችግሮች አንዱ መሆኑ በየጊዜው ተነግሯል።

፪ኛ/ በብዙ አገሮች ሆድን ለመሙላት ያህል የሚበቃ ምግብ ቢገኝም ለሰው የተሟላ ጤንነት በየቀኑ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን ማግኘት ችግር እየሆነ በመሔድ ላይ ነው።

፫ኛ/ የገለልተኛነታችንን አቋም በማያጠራጥር መንገድ በሥራ ላይ አውለን ብሔራዊ መብታችንን በማይነካ ወዳጅነት ከተቀራረብን ብዙ የርሻ ሥራ ውጤታችንን ጉረቤቶቻችን ለሆኑ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ልናቅርብ እንችላለን።

፬ኛ/ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ራሳችንን እየደጋገመ ካጠቃንና ከመጀመሪያው ክፉ ጠላት ከረኀብ ነፃ በመውጣት የመጀመሪያውን ብሔራዊ የኢኮኖሚ ድል እንቀዳጃለን።

፭ኛ/ የግብርና ሥራ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የራሱ ሊቃውንት ቢኖሩትም አብዛኛው ክፍሉ ፊደል ባልቈጠሩ ሰዎች ሊከናወን ስለሚችል ሌላው ጤነኛ ሥራ ፈት ቀርቶ የደከሙ አካለ ስንኩላንና በዕድሜያቸው የገፉ አረጋውያንና አረጋውያት ሊካፈሉበት ይችላሉ።

፮ኛ/ የርሻ ሥራ በዓመት ብቻ ሳይሆን በወራት ውስጥ ውጤቱን ስለሚያበረክት ከማንኛውም ሥራ ይልቅ ፈጥኖ ደራሽ ነው።

እንግዲህ ሀገራችን የርሻ ውጤቷን

ሀ/ በብዛት

ለ/ በጥራት

ሐ/ በዓይነት አሻሽላ ብታቀርብ በሀገሯ ረኀብን በማጥፋት ሳትወሰን ከፍተኛ የሆነ የውጭ ገንዘብ ልታገኝበት መቻሏ አያጠራጥርም ማለት ነው።

እርግጥ ነው እንደማንኛውም የገበያ ሁኔታ ሁሉ አንዳንድ ዓይነት የርሻ ውጤቶች ገበያም

በየጊዜው የሚለዋወጥ ነው። ስለዚህ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ድርጅቶችና የነጋዴዎች ምክር ቤት የዓለምን የገበያ ሁኔታ እያጠኑ በየጊዜው ለገበሬዎች ምክርና መግለጫ በመስጠት የሀገራችን የግብርና ሥራ እንደ ጊዜ ሁኔታ እየተራመደ በዓለም ገበያ የተሟላ ተወዳዳሪነት እንዲኖረው ለማስደረግ መጣጣር ያስፈልጋቸዋል።

በዚህ መንገድ ሕዝብና መንግሥት ለርሻ ተቀዳሚነት ሰጥተው ከተራመዱ ሀገሪቱ በርሻ ሥራ ውጤት ብቻ ገቢ ልታገኝ ትችላለች ማለት ነው። ገንዘብ ከተገኘ ደግሞ ብዙ ነገር ማግኘት ይቻላል።

ሀ/ ትምህርት ቤቶችን ክሊኒኮችን ሆስፒታሎችን መንገዶችን ድልድዮችን በሰፊው እንሠራለን።

ለ/ ልጆቻችንን በሙሉ ወደ ትምህርት ቤቶች ለመላክ እንችላለን።

ሐ/ ወንዞቻችንን እየገደብን ይህ በማይቻልበት አካባቢዎች ጉድጓዶችን እየቆፈርን ሰው ሰራሽ ሐይቆችን እየሠራን ለሚፈለጉበት ጥቅም ሁሉ እናውላቸዋለን።

መ/ በምድራችን ውስጥ ተቀብረው የኖሩ የማዕድን ሀብቶችን ህሉ በሀብታችንና በዕውቀታችን ከምድር በላይ እያዋልን ልጠንቀምባቸው እንችላለን።

ሠ/ ቀላልና ከባድ እንዱስትሪዎችን እናስፋፋለን።

እነዚህ ተግባሮች መፈጸም በኋላ ኢትዮጵያ ሠለጥኑ ከሚባሉት አገሮች ጎን ትሠለፍና የወደፊት

ሩጫዋን ትቀጥላለች። የሕዝቧ አኗኗር መልክ በፍጹም ይለወጣል። ጥሩ ቤት ጥሩ መኪና ልጅን ወደ ሚያስፈልገው ትምህርት ቤት መላክ ቢታመሙ ወደ ጥሩ ሆስፒታል ገብቶ መታከም በቤት ውስት ወሀ መብራት ማስገባት የሬዲዮ የቴሌቪዢን የለስላሳ የአልጋና ወንበር የማቀዝቀዣ የስልክ አለፍም

ሲል የግል መኪና ባለቤት መሆን በዘርና በሥልጣን ለተመረጡ ወይም ለከተማ ኗሪዎች ብቻ የተለዩ ጸጋዎች መሆናቸው በፍጹም ይረሳል። በገጠር ይኑሩ በከተማ ሹም ይሁኑ መንገድ ጠራጊ በትጋትና በቅንነት የሚሠሩ ሰዎች የላባቸውን ዋጋ እያገኙ የተቀራረበና የተመጣጠነ ኑሮ ይኖራሉ።

ሥራ የተባለ ሁሉ በየመልኩ ታላቅ ክብር ይኖረዋል። የርሻ ሥራ አሁን ካለው መልክ በፍጹም ይለወጣል።

፭ኛ/ አንድ ሰው የርሻን ሥራ ዓይነቶች በሙሉ ራሱ ብቻ ልሥራ ማለቱን የሚረሳበት ቀን ይመጣል።

ሀ/ አንድ ገበሬ ራሱ እህል አብቃይ ከብት በግ ፍየል ዶሮና ንብ አርቢ መሆኑ ይቀርና አንዱን ዓይነት ሥራ በሚገባ ያስፋፋል። ሌላው ቀርቶ በከብት ርቢ ሥራ ውስጥ የወተት ከብቶችንና የሥጋ ከብቶችን የሚያረቡ ገበሬዎች የተለያዩ ይሆናሉ።

ለ/ እንደ ማንኛውም የሠለጠነ ሕዝብ ሁሉ በየመንገዱ ጥግ በቂ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች ስለሚኖሩና እያንዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ወተት ቅቤ ሥጋና ሌላም የምግብ ዓይነት ስለሚያገኝ ሁሉን ከቤተ ላግኝ ብሎ ጉለብቱንና ሐሳቡን በተለያየ አቅጣጫ ያበክን የነበረበትን ልማድ ትቶ አንዱን ዓይነት ሥራ በዘመናዊ መልክ እያሻሻለ ይሠራል።

ይኸም ሲለመድ አንድ ገበሬ አባት ራሱ ወደ እርሻ ሥራ ሲሔድ ልጆቹ - ሴቶች ሕፃናት ሳይቀሩ

ሕፃናት ሳይቀሩ ጥቂት ወይም አያሌ የከሱ እንስሳትን እየተከተሉ ሲዞሩ መዋላቸው ቀርቶ ወደ ትምህርት ቤቶች ይሔዳሉ።

መ/ እያንዳንዱ ገበሬ ሥራውን ለይቶ ይዞ በዘመናዊ ዘዴ ሲሠራ የድካሙ ፍሬ የእጥፍ እጥፍ እየሆነ ይሔዳል። ለምሳሌ በደንብ ያልተጠበቁና ያልተሻሻሉ አንድ መንጋ ከብቶች እያንጋጋ ሊገኝ ከሚችለው የወተትና የሥጋ ውጤቶች ይልቅ በሚገባ ተመርጠውና ተዳቅለው በሚገባ ተጠብቀው ከሚገኙ ጥቂት ከብቶች እጅግ የበዛ ጥቅም ሊገኝ ይችላል።

፪ኛ/ ሰዎች «ለለት ጉርሳቸው ለዓመት ልብሳቸው» ጭረው በተወለዱበት መንደር መኖርን እንደታላቅ ነገር ማየታቸው ይረሳል።

ሀ/ ሰዎች ሁሉ በተለያየ ሙያ እየሠለጠኑ በመላው የሀገራቸው ክፍሎች በመዘዋወር ስለሚሠሩ ያንድ አባት ውለታ በድንበር ግፊያ በትውልድ መካካድ በግዥ ሥነ ሥርዓት አለመሟላት በግብረ ጠልነትና እነዚህን በመሳሰሉ ምክንያቶች ከከፍተኛ የሙግት የደጀ - ጠኝነት በሽታዎች ጋር የተያያዘ ትንሽ የመሬት ቁራሽ ማውረስ መሆኑ ይቅርና ሰፊዋን ርስቱን ኢትዮጵያን የተሻለች አገር አድርጎ ማስረከብ ይሆናል።

ለ/ በየአቅጣችዎቹ ታላላቅ አውራ ጐዳናዎች ሲከፈቱ የመመለሻ ድርጅቶች በጣም ሲሻሻሉና ሲስፋፉ አሁን የተራራቁ መስለው የሚታዩት ክፍለ ሀገሮች እጅግ ይቀራረባሉ። በየክፍሉ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም ጨርሰው መተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ፈጽመው ተቀላቅለው የጎሳ ስሜትን የክፍለ ሀገር ልዩነትን ይረሳሉ። ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ማንኛውም የሠለጠነ ሕዝብ ሁሉ ምኞቱና ዓላማው ከገደብ በላይ ይሆናል። የተፈጥሮ ኃይሎችን ምሥጢር በድፍረት እየተጋፋ አካባቢውን የሰው ልጆችን ኑሮ ያለማቋረጥ ለማሻሻል ይታገላል።

ለዕድገታችን የሚደረገው ትግል ከሚጀምርበት ጊዜ አንሥቶ የአካቢ ዓየር ወንዞች ምንጮችና

ሐይቆች በቁሻሻና በጢስ በሌላም ነገሮች እንዳይበከሉ የተራቆቱ ክፍለ ሀገሮች ወደ ለምለምነት እንዲመለሱ ተገቢ ትግል ይደረጋል።

የተፈጥሮ ኃይሎችን ጨርሶ መቆጣጠር ባይቻልም በጣም በሠለጠኑ ነገሮች ሌላ ቀርቶ በረዶ ወርዶ በሰብል ላይ ጥፋት ከማድረሱ በፊት በዓየር ላይ ሟሙቶ እንዲቀር በድርቅ ጊዜ ደመና ተሰብስቦ ዝናም እንዲቀጥል ለማድረግ በዘመናዊ የሳይንስ ምርምር የተደገፈ ብዙ ጥረት እየተከናወነ ጠቃሚ ውጤት በመስጠት ላይ ነው።

በአሁኑ ጊዜ የሰው ልጅ እጅግ ተራቋል። በዚያው ልክ ኑሮው እጅግ ተሻሽሏል። እኛን ኑሮ በጣም ከሠለጠኑት ሕዝቦች ኑሮ ጋር ስናስተያየው በመጠኑ ተመቸው የምንለው መካከለኛ ኢትዮጵያዊ የኑሮ ምቾት ያነሰ ሁኖ ሰለሚገኝ ለጥረታችን ለኅብረታችንና ለምኞታችን ገደብ ልንሰጠው አይገባም።

ምንም የሕይወት መሻሻል እንዳይኖረን እጅ እግራችንን አሥረው የኖሩትን ደካማ ልማዶች ሁሉ ጨርሰን መደምሰስ አለብን።

ከእንግዲህ ግባችን ባጭሩ ሲገለጽ ይህ ከሆነ ዘንድ ስለየግል ቁራሽ ርስታችን የነበረንን - ሙግት - የጭቅጭቅ የሐሳብ - የጠባብነት የድኅነት ሥራን ያለማሻሻል ልማድም በፍጹም መለወጥ አለብን።

ይህንንም ስናደርግ በቅርብ ጊዜ ኑሯችንን ማሻሻል ብቻ ሳይሆን ለውጣችን ፍጹም ሰላማዊ ይሆናል። መንግሥት ማለት ሕዝብ መሬት ማለትም የማይሸጥ የማይለወጥ የአንድ አገር ሕዝብ መንግሥት ለመላው ሕዝብ ደኅንነት በሚያውልበት መንገድ ሁሉ በቀጥታ የሚያዝበትና የሚጠብቀው እስከ ኅልፈተ ዓለም በመከታተል የሚመጡ ትውልዶች ቋሚ ሀብት መሆኑን ማንም ይረዳዋል።

ቀደም ሲል እንደገለጽሁትም መንግሥት ከአሁን ጀምሮ ስለ መሬት ይዞታ ወደ ምንፈልገው ግብ በሰላማዊ መንገድ የሚደርሱንን ዋና ዋና ተግባሮች በቀጥታ በሥራ ላይ ማዋል አለበት።

፩ኛ/ በደቡባዊ ኢትዮጵያ ታላላቅ መሬት ዘራፊዎች በሥልጣን በጉልበት እየተመኩ በሌላም ዘዴ እያጭበረበሩ የያዙትን ሰፋፊ መሬት በቀጥታ ወርሶ በመንግሥት እጅ ካለው ጋር ማቀላቀል

፪ኛ/ በግል ባለ መሬቶች ላይ ሰፍረው የሚገኙ ጢሰኞችን እያስነሡ በመንግሥቱ መሬት ላይ ማስፈር

፫ኛ/ ስለ መሬት ግብር የነበርው ለምለም - ከጠፍ የሚባል ነገር ሳይኖር አንድ ሰው የመሬት ይዞታው ከፍ ባለ መጠን እያደገ የሚሔድ ከባድ ግብር እንዲከፍልና ሊጠቀምበት አለመቻሉን እየተረዳ በፈቃዱ እንዲለቅ ማድረግ

፬ኛ/ መንግሥት መሬትን ለገበሬዎች መሥራት በሚችሉት መጠን የሚሰጠው በግል ርስትነት ሳይሆን በኮንትራት ሁኖ የግል ባለ መሬቶችም እንዳይሸጡ እንዳይለወጡ በአዋጅ ማገድ

፭ኛ/ በሰሜናዊው ክፍል መንግሥት ለጠቅላላው ሕዝብ ዕድገት የሚፈልገው ማንኛውም መሬት በላዩና በውስጡ ካለው ነገር ሁሉ ጋር መንግሥት በቀጥታ የሚያዝበት መሆኑን እንዲያውቅ ማድረግ

፺ኛ/ በማንኛውም ከተማ የሚገኝ ቦዘን መሬት ሁሉ የችርቻሮ ዕቃ መሆኑ ቀርቶ በየማዘጋጃ ቤቶች ቁጥጥር ሥር ሁኖ ለሚያስፈልጉ የሕዝብና የመንግሥት አገልግሎቶች እንዲውል ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ጉዳዩ የሚመለከተው ሕዝብም ለውጡ የራሱ ለውጥ በውጤቱ የሚገኘው ጥቅምም ጥቅም መሆኑን ተገንዝቦ በሙሉ ልቡ እንደ ሚተባበር ሙሉ እምነት አለኝ።]

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቢሆን ለግሉ የዕለት ትንሽ ጥቅም ሲል ራሱ ጨምሮ የሚጠቅምበትን ከፍተኛ ብሔራዊ ጥቅም ይቃወማል ብዬ አልጠራጠርም።

ሀገራችን እጅግ የምታሳዝን ምስኪን እናታችን ናት። ሁላችንም በያለንበት እሷን ለማዳን እንሰለፍ። ያለዚያ ሁላችንም የምናሳዝን የሙት ልጆች እንደሆንን እንኖራለን። ለልጆቻችን የምናወርሳቸው ሀብትም የሚያኮራ ርስት ሳይሆን ችግር በሽታ ድንቁርና ውርደትና ኃፍረት ብቻ ይሆናል። ለሁላችን ደኅንነት የመጣልንን ለውጥ እንደ ጠላት ዐይተን የዓለም ሕዝብ መዘባበቻ እንዳንሆን ችግራችንን ድል ለማድረግ እንተባበር።

# መድረሻ

በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ከታተመው «ሬትና ማር» ከሚለው የግጥም መጽሐፌ የወሰድሁት።

ምንም ሕልም አይደለም።

ድንገት ጋደም ስል በደከምው ጐኔ

ሲዞር ይታየኛል ታላቅ ነበር ባይኔ።

ያ አጉል ዘር ከፋፋይ ጉረኛው ፈላስፋ

በወንድሞች መሐል መርዝ እንዳያስፋፋ

ታርሞ ተነቅሎ ከሀገር ሲጠፋ

ያገር ዕድገት ጠላት የዕድል አሳዳጅ

ጥቅምን ሁሉ ሊያንቅ እንዲያ ሲጐመጅ
በግራ በቅኙ እየዘረጋ እጅ
ሌላውን ሁሉ ገድሎ ለራሱ እሚያበጅ
የጥቅሙ ተካፋይ ሳይሆን አማላጅ
በወንጀል ተከቦ ፈርዶበት ፈራጅ
ሲማቅቅ ሲከርም ሲማቅቅ ሲባጅ
ሲባል የሕብ ጠላት የሰይጣን ወላጅ
በሌላ እንኳ ሳይሆን በሥልጣን ሰበብ
የሣንቲሟን ግማሽ የቀማ ከሕዝብ
እንደ ሠረቀ ሰው የመንግሥት ገንዘብ
በሰንሰለት ታሥሮ ታጅቦ በዘብ
ቅጣቱን ሊቀበል ፍርድ ቤት ሲቀርብ
የኢትዮጵያ ሕዝብ ከልብ ተቀራርቦ
ባንድ ቃል ተናግሮ ባንድ ልብ አስቦ
የጠላቶቹን አፍ ዘግቶና ሸብቦ
አብሮ የዘራውን ባንድ አብሮ ሰብስቦ
ሳይኖር ራብተኛ ሁሉም እህል ጠግቦ
በኢትዮጵያ ወገብ እንደመቀነት
የተጠመጠመው ለምለሙ መሬት
ከወባ ተላቆ ህዝቡ ሰፍሮእብት
ባለም ታይቶ እማያውቅ የሰሊጥ ብዛት
የጫኝ ያለህ የሚል ጉድ የጥጥ ጭነት
የጤፍ የበቆሎው የስንዴውም ምርት


ተትረፍርፎ ሲቀር ካመት እስካመት
እንደ ተነበዩት ቀድመው ሊቃውንት
አገራችን ሁና የዳቦ ቅርጫት
ለሩቅ ወዳጅና ለቅርብ ጐረቤት
እስከቻለን ድረስ ሁሉም ሰው ተምሮ
ማብራሪያ ተሰጥቶት በዐዋቆች ተመክሮ
ራሱም አስቦ ሁሉን ተመራምሮ
ሙግት ጭቅጭቅን ወዲያ ጥሎ አንቅሮ
እግዜር እንዳዘዘው አንዱ አንዱን አፍቅሮ
ራሱም እንዳየው በለመደው ኑሮ
ባንድ አብሮ እርሻን አርሶ ባንድ አብሮ መንጥሮ
ባንድ አብሮ አጨዳ አጭዶ ባንድ አብሮ ከምሮ
አንዱ ሲዳር አንዱ ዘፍኖ አንዱ ሲሞት ቀብሮ
ስኖር በደስታ ከብሮ ተከባብሮ
ሁሉም ወገናችን ምሥጢሩ ገብቶት
ለመደሩ አሠራር ቅጥ መጠን ሰጥቶት
የጋራ መሬቱን ያባቱን ርስት
ደረቁን ለመንድር ሜዳውን ለከብት
ለምለሙን ለእህሉ ጓሮውን ላትክልት
ከፋፍሎ መድቦ ሠርቶ ባንድነት
የመንግሥት እርዳታ በቀላል ደርሶት
ታማሚው መድኃኒት ሕፃኑ ትምህርት
ሳይወጣ ሳይወርድ ሲያገኝ በወቅት

ተምሮም ሲሠራ ሥርቶ ሲያገኝ ሀብት
ሲረሣ ግሙ ዕድል መሆን ሥራ - ፈት
በዐራቱ ማዕዘን በለምለሙ ሜዳ
የወዳደለ ከብት ብዙው ቀንዶ - ጐዳ
ግማሹ ለወተት ሌላው ለፍሪዳ
ከዚህ ላይ ፍየሏ ከዚያ በጓ ወልዳ
የታከመው መንጋ ጤናው ያልተጎዳ
ጠግቦ እየፈነጨ ወደቤት ሲነነዳ
የንዱስትሪውና የርሻው ውጤት አብሮ
በከባድ መኪና በባቡር ተሳፍሮ
በዓለም ሁሊ ሊናኝ ሲጫን በመርከብ
ብዙ ለውጥ ሊያመጣ ወይንም ገንዘብ
ታላላቁ ወንዞች ዓባይ አዋሽ ባሮ
ተከዜ ነዋ ዋቢ? ምኑስ ምን ተቈጥሮ!
ለሐበሾች ጥቅም ኃይሉ ተወስኖ
ግማሹ ለጉልበት ግማሹ ለመብራት ሌላውም ለመስኖ
ይውልና ሁሉ በየመልኩ ሁኖ
ብርሃን ብቻ ሁኖ ገጠሩ ከተማው
በሁሉም ቀን ሲሆን ተገፎ ጨለማው
በጭራሽ ሲረሳ ኩራዙና ሻምው
ናፍጣ ችርቻሮ ሥራ መሆን ሲቀር
በከተማ ኪዎስክ እንዲሁም በመንደር
በዚያም በዚህም በኩል ሲያንጐራራ ፋብሪካ

መሬትን ሊያስወልድ ቆፋሪው መኪና ዘቅዝቆ ሲያሽካካ
ጐበዙ ሠሪ ሕዝብ ባገሩ በሥራው በኑሮው የረካ
«ወዮለት! ጠላት እርሷን ለሚነካ!
ታላቋ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!» እያለ ሲያወካ
ይኸ ብቻ አይደለም ከዚህ የሚበዛ ይኸን የመሰለ
ዞትር እየመጣ ባኔ ላይ ተሳለ።
ይህ አጉል ሕልም ይሆን የምኞት ቅዥት
ዓለም እስከምታልፍ የማንደርስበት?
ወይስ የሚቻል ነው የፈጠጠ እውነት?
የሚያደክም ምክር የባዕዳን ትንቢት
ሳይኖረን ሳይገባን ሐኬት
አብረን በማስወገ ያለብንን ችግር
ሁላችን ከሠራን ባንድ ልብ ላንድ አገር
ምኑም ሕልም አይሆንም ከዚህ ሁሉ ነገር።
የምዕራብም ሰዎች ይኸነን ከሠሩ
የምሥራቅም ሰዎች ይኸነን ከሠሩ
በኛስ አገር ቢሆን ምንድን ነው ችግሩ
ሕዝቡ ተባባሪ ባለጸጋ ምድሩ።

ኢትዮጵያ ትቅደም

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

አቤ ጉበኛ (፲፱፻፳፫ ዓ/ም በባሕር-ዳር አካባቢ፣ ይስማላ ጎጃም ተወልደው - ፲፱፻፸፪ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ አረፉ። ባለቅኔ፤ ደራሲና ገጣሚ የነበሩት አቤ ጉበኛ በስድስት ዓመት ፊደል ቆጥረው ንባብ ከተማሩ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሲከታተሉ ቆዩ። ከዚያም ወደ ደንጎላ ሄደው በቢትወደድ መንገሻ ጀምበሬ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል።

አቤ ጉበኛ የመጀመሪያ ሥራቸው በማስታወቂያ ሚኒስቴር ሲሆን ቀጥሎም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተቀጥረው በመንግሥት ሥራ ለስድስት ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ ሕይወታቸውን በአብዛኛው የገፉት በደራሲነት ነው። በ1967 እ.ኤ.አ. በአዮዋ ክፍለ-ሀገር ወደ ዓለም አቀፍ የጽሑፍ ህብረት ፕሮግራም (International Writing Fellowship Program) ሄዱ።

<u>የደራሲው ሥራዎች፡-</u>

1. መስኮት **(ግጥምና ቅኔ)**
2. እሬትና ማር **(ግጥምና ቅኔ)**
3. ከልታማዋ እኅቴ **(ልብ-ወለድ)**
4. ምልክዐም ሰይፈ ነበልባል **(ልብ-ወለድ)**
5. አንድ ለናቱ **(ታሪካዊ ልብ-ወለድ)**
6. የረገፉ አበቦች **(ልብ-ወለድ)**
7. ከመሰፍት ሠራዊት፥ ይጠንቀቅ ሰውነት **(ተውኔት)**
8. ቂመኛው ባሕታዊ **(ተውኔት)**
9. የሮም አወዳደቅ **(ተውኔት)**
10. የራሔል ዕንባ **(ተውኔት)**
11. የደካሞች ወጥመድ **(ተውኔት)**

12. አልወለድም (፲፱፻፶፫ ዓ.ም.) **(ልብ-ወለድ)**
13. የዓመፅ ኑዛዜ (፲፱፻፶፫ ዓ.ም.) **(ልብ-ወለድ)**
14. መሬት የማን ነው
15. The Savage Girl 1964 እ.ኤ.አ. **(በእንግሊዝኛ)**
16. Defiance 1975 እ.ኤ.አ. **(በእንግሊንግሊዝኛ**)